

## ገበሬው የተሻለ ዋጋ ለማግኘትና ለመደራደር ራሱን በመረጃ አስታጥቋል

እሌኒ ገብረ መድህን (ዶ/ር)

4

## «ኢህአዴግ አዳዲስ የህዝብ ግንኙነት ባለሞያዎችን አስፈረመ!»

## «ተባለ ... ተባለንዴ?!»

አቤ ቶኪቻው

10

## ጥምረት ለአስተማማኝ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት

ታምራት ታረቀኝ

9





# አውራምባ ታይምስ

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

2ኛ ዓመት ቁጥር 89 | ህዳር 01 ቀን 2002 | ዋጋ 3.50 ብር


# ማን ያተርፋል?




3

*ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም አራት የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ የስነ ምግባር ደንብ ሰነድ ተፈራርመዋል:: ሰነዱን ከፈረሙት አራት የፓርቲ አመራሮች መካከል ግን የጠ/ሚ መለስና የኢ/ር ኃይሉ ሞቅ ያለ መጨባበጥ አነጋጋሪ ምዕራፍ ከፍቷል::* **ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም** «ስምምነቱ መለስን ምንም አያስከፍለውም፤ ኃይሉ ግን ተጨባጭ ውጤት ካላስገኘ ዋጋ ይከፍልበታል» ሲሉ በተለይ ሁለቱ ወገኖች የገቡበት ውል የተቃኘበትን ስሌት ከመንፈሳዊ ወኔ፣ ከተለመደው ብልጠትና ከፖለቲካ ብልሃት ጋር እያነፃፀሩ ይተነትኑታል::


በውስጥ ገፆች

«እንባ ጠባቂ» ተቋም፤ እንባ እያበሰ ወይስ ያልተጠየቀውን እየመለሰ?

ምርጫ ቦርድ ሥልጣኑን አልተነጠቀም፣ አልተጠቀመበትም እንጂ

*ከ540 በላይ አርሶ አደሮች:- «የንብረትና የአካል ደህንነት መብታችን ተገፈፈ» ሲሉ ለጠ/ሚ/ሩ አመለከቱ*

የመድረክ አገራዊ ዓላማ በአፍራሽ ጽሁፍ አይቀለበስም


# የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች በዴሞክራሲ ያምናሉን?









6

## ኤዲቶሪያል

# ዜጎች ምርጫ በመጣ ቁጥር «ደግሞ መጣ» እያሉ ከተሸበሩ የዴሞክራሲ መገለጫነቱን ስቷል!

«ዓለም አንድ መንደር ሆናለች» በሚባልበት የቴክኖሎጂ እመርታ ዘመን በመላው ዓለም ያሉ አገራት የሚያከናውኗቸው ተግባራት «የግል ጉዳዬ» የሚል ጽንፈኛ ክልከላ የማይደረግባቸው ሆነዋል:: የአደጉ አገራት በዚህ የቅርብ ጉረቤታምነት መርህ እጅ ለእጅ ተያይዘው ማህበራዊ ለውጥ፣ ኢኮኖሚያዊ እድገትና የሰለጠነ ፖለቲካ ለማካሄድ የሚያስችል ደረጃ ላይ የደረሱ ሲሆን አፍሪካን ጨምሮ አብዛኞቹ በማደግ ላይ ያሉ አገራት ደግሞ ከዚህ ትሩፋት በእጅጉ ፈቀቅ በማለት በሚከተሉት አምባገነናዊ ስርአት ዜጎቻቸው በድህነትና በምግብ እጦት ስጋት ውስጥ እንዲኖሩ፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዳሻቸው እንዲጣሱ በአጠቃላይም የፖለቲካ አለመረጋጋት እንዳይሰፍን አድርጓል:: «ያደጉት» ከስህተቶቻቸው ሲማሩ፣ ጠንካራ ጎናቸውን ሲያጎለብቱ «በማደግ ላይ» ያሉት ደግሞ ዘወትር ከስህተቶቻቸው ጋር ሲኖሩ፣ ጠንካራ የተሰኙ ልምዶቻቸውን ሲያመክኑ እንመለከታለን:: ለበጎ የተባጁ ጅምሮቻቸው እንኳ በደም መፋሰስና በማሕበራዊ ቀውስ የሚቋጩበት ጊዜ የትየለሌ ነው:: አገራችንም በዚሁ «የማደግ ላይ» ማዕቀፍ ውስጥ ትገኛለች::ይህም በማደግ ላይ ያሉ አገራት ያሉባቸውን አሉታዊ መገለጫዎች እንድትጋራ አድርጓታል:: ማንኛችንም ብንሆን አገራችን በዚህ አዙሪት ውስጥ እንድትሽከረከር አንፈልግምና የምንለውን ልንል ወደድን::

ከስህተቶች ያለመማር፣ ገንቢ ተሞክሮዎችን ማምከን፣ በጎ ርዕይ ተሰንቆባቸው የተጀመሩ ተግባራትን በጥፋት መቋጨት ውጤቱ ለህግ የበላይነት መጣስ፣ ለድህነትና ፖለቲካዊ ያለመረጋጋቶች መንገድ ይከፍታል:: የስልጣኔ ፈር ቀዳጅና እድሜ ጠገብ የመንግስትነት ታሪክ ያላት ኢትዮጵያ መሪዎች ምን ስህተቶችን ፈፀሙ፣ ምን እድሎችን አመከኑ፣ እንዲሁም ቢሳኩ ሌሎች የደረሱበት ሊያደርሱ ይችሉ የነበሩ ምን በጎ ጅምሮችን በአሉታ ቋጩ? ብንል ስፍር ቁጥር የሌላቸው ምሳሌዎችን መደርደር ይቻላል:: አላማችን ግን ሶስት ሺህ ዘመን ወደኋላ የሚያስከነዳና የየራሱ መገለጫ ያለውን የአሉታ ገመና መዳሰስ አይደለም:: ካወቅንበት ማሕበራዊ ለውጥ፣ የኢኮኖሚ እድገትና የፖለቲካ መረጋጋት የሚያቀዳጀን እድል አሁንም ከፊታችን ይጠብቀናል ለማለት ነው::

በእርግጥ ካወቅንበትና ፈቃደኞች ከሆንን በየዕለቱ እንዲያውም በየሰዓቱ ታላላቅ አገራዊ እድሎችን የሚወስኑ ጉዳዮች በእጃችን ላይ ያርፋሉ:: የእነዚህ ሁሉ እድሎች አተገባበር ለዘላለም እንድትኖርልን የምንመኝላትንና ተስፋ የምናደርግባትን አገራችንን እጣ ይወስናሉ:: ታላላቅ ክንውኖች የሚመጡት ግን በዓመታት ውስጥ ነው:: ከእነዚህ በዓመታት ውስጥ ከሚመጡ ታላላቅ ክንውኖች አንዱ ህዝቦች በድምጻቸው መሪዎቻቸውን የሚመርጡበት አገር አቀፍ ምርጫ ሲሆን የሚፈፀምበት ጥብቅ መርሕም ከላይ የተመለከትናቸውን የመሆንና ያለመሆን እጣ ይወስናሉ:: ከጥቂት ወራት በኋላ ይካሄዳል ተብሎ ስለሚጠበቀው ብሔራዊ ምርጫም

አገራችን ከስህተቶች ባለመማር፣ ገንቢ ተሞክሮዎችን በማምከንና ተስፋ ተሰንቆባቸው በአሉታ ሲቋጩ ከኖሩ አፍራሽ ድግግሞሽ እንድትወጣ ከፈለግን፤ ደግሞም ካወቅንበት መፍትሔው በእጃችን መሆኑን ለማስታወስ እንሻለን::

የምርጡኝ ቅስቅሳ ተደርጎ፣ የተመራጮቹ ማንነትና የምርጫው ሂደት የራሱ ነባራዊ እውነታ ስለነበረው የ1950ዎቹ የሕዝብ ወኪሎች አመራረጥ ማንሳት ሳያስፈልግ ከአምስት አመታት በፊት ስለተፈፀመው አገር አቀፍ ምርጫ የተለያዩ ተሞክሮዎችን በማስታወስ በእጃችን ላይ ስላለው ሌላ ዙር ታላቅ ክንውን መዳሰስ ይኖርብናል::

በ1997 ዓ.ም የተደረገው አገር አቀፍ ምርጫ በኢትዮጵያ የምርጫ ታሪክ የተለየ ነው ያስባሉት አጀማመሮችም አፈፃፀሞችም እንደነበሩት ይታወሳል:: ከሁሉም ገዝፎ የሚታየው ሕዝቡ በአገሩ ፖለቲካዊ ጉዳይ በከፍተኛ ተነሳሽነት ተሳትፎ ያሳየበት መሆኑ ነው:: ዘር ተቆጥሮ ዙፋን የሚወርስበት፣ ያም ካልሆነ መፈንቅለ ስልጣን የሚካሄድበት ጎታች ስርአት እንዳበቃለት ወይም ሊያበቃለት እንደሚገባ በሙሉ ልቡ አምኖ የገባበት አጋጣሚ ነበር:: «ፋኖ ተሰማራ» ብሎ ጫካ መግባት ሳያስፈልግ፣ የወንድማማቾች ደም ሳይፈስ በድምጽ ብቻ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ማድረግ ይቻላል ብሎ ያመነበትና የቤት ሥራውን በተገቢው መንገድ ያከናወነበት ነበር ብለን እናምናለን::

ይህ ከፍተኛ ተነሳሽነትና ተሳትፎ በስጦታነት የቀረበለትና በአንድ ጀምበር የመጣ ግን አልነበረም:: ዘመናት የፈጀ ዋጋ የከፈለበት፣ ጥቅሞቹንና ፍላጎቶቹን አውቆ ሲያራምዳቸው ቢቆይም በመሪዎቹ አፋኝነት፣ በተፎካካሪዎቹ ያለመቀናጀትና በሌሎችም ጎታች ሁነቶች እግር ተወርች ታስሮ ለግማሽ ምዕት ዓመት ሲመክንበት የኖረው ተስፋው ነበር:: ተሳትፎውን ለማጎልበት በገዢው ፓርቲም፣ በተፎካካሪዎችም፣ በሚዲያ ተቋማትም በገንቢነታቸው የሚዘከሩ ሥራዎች ተሰርተዋል:: በዚህም ከ26 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ለመራጭነት የተመዘገቡበት ሪከርድ ተመዘገበ:: ከ36 ሺህ በላይ የምርጫ ጣቢያዎች ዝግጁ ሆኑ:: ሌላም ታሪክ የማይሽረው መልዕክት ተላለፈ::

ዜጎች ለሚደግፏቸው ፓርቲዎች አጋርነታቸውን አደባባዮችን በመሙላት አሳዩ:: በዚህ ወቅት እጅግ የከበረው ኢትዮጵያዊ የስብዕና መገለጫ ለአገር ንብረት፣ ለሌሎች አመለካከትና አማራጭ ክብር በማሳየት ፖለቲካ የገባው፣ የዴሞክራሲን አቡጊዳ አስቆጣሪ የማይፈልግ ትወልድ መኖሩን አረጋገጠ:: ይህ ፖለቲካዊ ንቃት ህሊናና ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርን የመሻት ዝማሜ በድምጽ መስጫው እለትም ለሰጠው ድምጽ ዘብ በመቆም ተረጋገጠ:: እናም ምርጫው ተጠናቀቀ:: ሕዝቡ ድርሻውን ተወጥቶ ቀሪውን ኃላፊነት ለተወዳዳሪዎቹ ሰጠ:: ውጤቱ ምን ነበር? ከሂደቱ ያገኘነው ገንቢ ተሞክሮ ምን ነበር? ምን ነበር ያመከንነው? የተሳሳትነውና ከዚህ ስህተት ልንማር የምንችለው? እንደሕዝብ ልንጠይቅ ምላሽም ልናገኝለት ይገባል::

ውጤቱ በምርጫ ታሪክ ውስጥ ተፎካካሪዎች ከፍተኛ የውክልና ድምጽ ያገኙበት ቢሆንም ያልተጠበቁ ጉዳቶችን ያስከተሉ ውዝግቦች ተፈጠሩ:: ለቀውሱ የትኛውም ወገን የበለጠ ድርሻ ይኑረው ኢትዮጵያ በመቶዎች የሚቆጠሩ ልጆቿን ሕይወት አጣች:: መጠናቸው በትክክል የማይታወቅ ዜጎች ለእስር ተዳረጉ:: አንድ ቢሊዮን ብር የሚያወጣ ንብረት ወደመ::

የጉዳቱ ሌላ ጎን ደግሞ ለበጎ አላማ የተባጀው ሂደት ባጋጠመው ምስቅልቅል የዜጎች ስነ-ልቡና የሰፈነበት አሉታዊ ስሜት ነው፡፡ መራጩ ሕዝብ ከዚህ ሁሉ ሁነት ጀርባ ለመብቴ ለነፃነቴና ለጥቅሜ ግንባራቸውን አያጥፉም ያላቸው አንዳንድ ወገኖች አሰላለፋቸውን ሲቀይሩ፤ ለችግረኛ ው ሕዝብ ሥራ ፈጣሪዎች ሳይሆኑ ክቡሩን ተልዕኮ መረማመጃ አድርገው ስራ ፈላጊዎች መሆናቸውን፣ ለገቡለት ቃል ኪዳን ታማኝ ከመሆን ይልቅ እንደጤዛ ረግፎ ከቀረ ስልጣን ማግስት እንኳ እንባውን ጠርጎ ትግሉን ከማጠናከር ይልቅ በየአስባቡ ተቆራቁሰው የሚለያዩ ሆነው ተገኙ፡፡ ተግባራቸው እየወቀሳቸው በየዕለቱ ይቅርታ የሚጠይቁ ሆኖም በየሰአቱ በስህተት ሽክርክሪት የሚዘፈቁ ሆኑ፡፡በድህረ ምርጫ በተወሰደው እርምጃም የደረሰውን ጉዳት አስመልክቶ ኃላፊነቱን ማንም ወሰደ ማን የሆነው ሁሉ የሆነው «ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!» ብለው ማሕበራዊ ለውጥ፣ ኢኮኖሚያዊ እድገትና የሰለጠነ ፖለቲካ እንዲመጣ በሚሹ ወንድማማቾች መካከል ነው፡፡ ስህተቱ ምን ነበር? እንበል፡፡

ስህተቱ ከልምድ ማጣት፣ የፖለቲካ ግልጽነት ካለመኖር፣ የሚመጣውን ውጤት ካለመጠበቅ፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ያለመጠናከርና እኔነትን መሰረት ካደረጉ ውሳኔዎች ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ በሰለጠኑት አገራት እንደሚደረገው ስህተቶች ከተፈጠሩ በኋላ ልምድ በመቅሰም፣ ግልጽና የጠራ ፖለቲካ በማራመድ፣ በግል ዝናና ጥቅም ዘውግ ዙሪያ ከመሽከርከር ለሕዝብ ጥቅምና መብት በመቆም፣ ከስህተቱ መማር በሂደቱ ካጋጠሙ ገንቢ ተሞክሮዎችም መኮረጅ ያስፈልጋል እንላለን፡፡

መጪው ምርጫስ? የሚል አነጋጋሪ ጥያቄ ይደቀንብናል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዝግጅት ምን ይመስላል? ህዝቡ በድምጼ የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር ማድረግ እችላለሁ የሚልበት የስነ ልቦና ዝግጅት አለው? ሌላ ዙር ቀውስ፣ የህይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት ላለመከሰቱ እንዲሁም በውዝግብ ጦስ ያልታሰቡ ጉዳቶች ላለመድረሳቸው «እርግጠኛ ሁን» የምንልባቸው ማሳያዎች ምንድናቸው? ስለዴሞክራሲና ስለህግ የበላይነት ብዙ ሊወራ ይችላል፤ በተግባር ግን የዴሞክራሲ ምሰሶዎችን የመነቅነቅ ሁኔታ ካለ፣ ዜጎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ ያለህግ ሰርአት የሚጉላሉ ከሆነ ወይም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በብቃት እንዲሳተፉ ካልተደረገ የማሕበረሰቡ ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች፣ ፍልስፍናዎችና ፍላጎቶች በነፃነት ካልተንፀባረቁ የምርጫ መደረግ መርህ አጠያያቂ ይሆናል፡፡

ግንቦት ወር አጋማሽ ላይ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀውን ምርጫ አስመልክቶ ብሔራዊ ም/ቦርድ የምርጫ ሰሌዳ ይፋ ያደረገ ሲሆን ገዢው ፓርቲና ሶስት ፓርቲዎችም የምርጫ ስነ ምግባር የመግባቢያ ሰነድ ፈርመው ከውይይት በኋላ ወደፓርላማው እንደሚላክ ገልፀዋል፡፡ ቀደም ሲል በ2000 ዓ.ም በወጣው ህግ መሰረት የምርጫ ስነ ምግባር ደንብን ከባለድርሻ አካላት ጋር አርቅቆ ወደፓርላማ የመላክ መብት በአዋጅ የተሰጠው ለምርጫ ቦርድ መሆኑን የገለፁ ፓርቲዎች ውይይቱን ለማቋረጥ ሲገደዱ ጉዳዩ በድምጽ ብልጫ ቦርዱ እንደመራው ሲደረግ አይተናል፡፡ በድምጽ ብልጫ ፓርቲዎቹ አወያይ ይሁኑ ቢባል ኖሮ ቦርዱ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን ተገፈፈ ማለት አልነበረም? የሚል ጥያቄ አስነስቷል፡፡ በውይይቱ ላይ ተሳታፊ የነበሩት ወገኖች ለኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋ ፈንጣቂና በመጪው ምርጫ በነቂስ ወጥቶ እንዲመርጣቸው የሚያደርግ ስራ ሰርተዋል? ሂደቱ ህዝቡን የስልጣን ባለቤት የሚያደርግ ወይስ ለፕሮፓጋንዳ

ፍጆታና ማዳመቂያነት የሚያገለግል? ራሳቸውን መፈተሽ የደረሱበትን እውነታ በግብታዊነት ሳይሆን በስነ አመክንዮ ማስቀመጥን ይጠይቃል፡፡

በየአምስት አመቱ ወቅቱን የጠበቀ ብሔራዊ ምርጫ እንደሚደረግ እናውቃለን፡፡ ያለፈው ምርጫ ምስቅልቅል ግን በተለይ የተቃውሞውን ጎራ በእጅጉ እንዳዳከመው እንገነዘባለን፡፡ ውድድር ተካሄደ የሚባለው በብቃት ሊፎካከሩ የሚችሉ ሁለትና ከዚያ በላይ ወገኖች ካሉ ብቻ ነው በሚለው መርህ መሰረት አሁን ያሉት ተፎካካሪ ፓርቲዎች ህጋዊ የፖለቲካ ፓርቲነት ሰነድ ከመያዝ በተጨማሪ ገዢውን ፓርቲ እናሸንፋለን ወይም በብቃት እንፎካከረዋለን የሚያሰኛ ቸውን፤ በስሜታዊነት የተዳሰሰ ሳይሆን በስነ አመክንዮ የተዋቀረ ምላሽ እንጠብቃን፡፡ ምርጫ የሚካሄደው በዘልማድ ሳይሆን በዴሞክራሲያዊ ህግጋቶች መርሕ ለላቀ አላማ ነውና፡፡ ይህ የላቀ አላማ የሕዝብን ሉአላዊነት፣ የህግን የበላይነት፣ መሰረታዊ የሰብአዊና የዴሞክራሲ መብቶች የሚያስጠብቅ ያለምንም የውጭ ኃይሎች «ኩርኮማ» ለመራጩ ህዝብ በሚኖረው ፋይዳ ብቻ በሚከናወን ፍትሃዊ ምርጫ የሚረጋገጥ እሴት ነው፡፡ ይህን የላቀ አላማ ለማሳካት የቀረው ጊዜ «በርበሬ ቀንጥሱ...» አይነት ማጣፍያውን አሳጥሮት ከሆነ በተገቢ ህጎች ማዕቀፍ አማካይነት ጊዜው የሚራዘምበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የድህረ ምርጫ ውዝግቦች ይከሰታሉ የሚል ተገቢ ጥርጣሬ ካለ ወቅታዊና ህጋዊ እርምጃ መውሰድ፣ ከምንም ነገር በላይ ደግሞ ለአገር እድገት፣ ለሕዝቦች ክብርና ለዴሞክራሲ መስፈን ባለቤቱ እያንዳንዱ ዜጋ መሆኑ ሊታወስ ይገባል፡፡ አገራችን ከስህተት የድግግሞሽ አዙሪት እንድትወጣ በጋራ እንቁም፡፡ ልዩነቶች በተጽእኖና በማስፈራሪያ ሳይሆን በህግና በውይይት ብቻ ይፈቱ፡፡ ዛሬንና እኔነትን መሰረት ያደረገ ሳይሆን ትውልድንና ሕዝብን የሚቤዥ ምርጫ እንጠብቃለን፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

## verbatim

«... እኛ እኮ ስራ ያለን ፓርቲ ነን፡፡ እያንዳንዱ ‘ የግል ጉዳይ አለኝ ’ ባለ ቁጥር ከዘጠና ፓርቲዎች ጋር መድረክ መክፈት አንችልም፡፡ ይህንን ለመድረክ ካደረግን ሌላም የግል ጉዳይ አለኝ ብሎ ሊመጣ ነው፡፡»

**አቶ ሴኩቱሬ ጌታቸው**

**የኢህአዴግ የሕዝብና የውጭ ግንኙነት ኃላፊ**

«መድረክ ለብቻው ከኢህአዴግ ጋር መነጋገር ይፈልጋል፣ ለምንድነው ኢህአዴግ

የሚፈራው?» በሚል ከሪፖርተር ጋዜጣ ለቀረበላቸውን ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፡፡

*«እነዚህ ሕጎች [የፕሬስ፣ የበጎ አድራጎት እና የፀረ-ሽብርተኝነት] ከፀደቁ በኋላ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ርግጠኝነት ማጣት መፈጠሩ እሙን ነው። … ይህም የምርጫ ሥነ ምግባር ሰነዱን አስፈላጊነት የበለጠ ያጠናክራል።»*

*ሚስተር ኖርማን ሊንግ*

*በኢትዮጰያ የእንግሊዝ አምባሳደር*

*«ሕጎቹ ዜጎች በምርጫው ላይ ጨለምተኝነት እንዲታይባቸው  በማድረጉ ከምርጫ 97 በፊት ከነበረው የተለየ ድባብ ፈጥረዋል፤ የእርስዎ ተስፈኝነት ከእውነታው አይጋጭም?»  በሚል ከአዲስ ነገር ጋዜጣ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ።*

*«ገና ኢህአዴግ እዚህ አገር ሲመጣ ለስልጣን ከተጠየቁት ሰዎች መካከል አንዱ ነኝ።… በፖሊሲው ስለማላምን እምቢ ብያለሁ። በደርግ ጊዜ የሰራሁት ፖሊሲውን ሳላውቅ ነው።»*

*ኢ/ር ኃይሉ ሻውል*

*የመኢአድ ፕሬዚዳንት*

*«ኢህአዴግ በርስዎ የማኔጅመንት ችሎታ የኮንስትራክሽን ሚ/ር ቢያደርግዎ ይቀበላሉ?» ሲል አዲስ አድማስ ጋዜጣ ጠይቋቸው በደርግ ጊዜ [ሚኒስትር የሆኑት]  ፖሊሲውን ሳያውቁ መሆኑን በማስታወስ የሰጡት ምላሽ።*

## ኮሜንተሪ

# በስምምነቱ ማን ያተርፋል?

**በመስፍን ወ/ማርያም (ፕሮፌሰር)**

**ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም አራት የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ የስነ ምግባር ደንብ ሰነድ ተፈራርመዋል። ረቂቅ ሰነዱን ከፈረሙት አራት የፓርቲ አመራሮች መካከል ግን የጠ/ሚ መለስና የኢ/ር ኃይሉ ሞቅ ያለ መጨባበጥ በኢትዮጵያ ፖለቲካ አነጋጋሪ  ምዕራፍ ከፍቷል። ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም በዚህ ጽሁፋቸው «ስምምነቱ መለስን ምንም አያስከፍለውም፤ ኃይሉ ግን ተጨባጭ ውጤት ካላስገኘ ዋጋ ይከፍልበታል» ሲሉ በተለይ ሁለቱ ወገኖች የገቡበት ውል የተቃኘበትን ስሌት ከመንፈሳዊ ወኔ፣ ከተለመደው ብልጠትና ከፖለቲካ ብልሃት ጋር እያነፃፀሩ ይተነትኑታል።**

---

አቶ መለስ ዜናዊ፣ ኢ/ር ኃይሉ ሻውል፣ አቶ ልደቱ አያሌውና አቶ አየለ ጫሚሶ የተፈራረሙት ስምምነት የሰሞኑ ዋና ወሬ ሆኖአል፤ ነገር ግን ከአነበብኳቸው ውስጥ በእኔ አስተያየት መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች የተነሳ አይመስለኝም፤ ለምሳሌ --

1. ተፈራራሚዎቹ እነማን ናቸው? አንድ የሰማሁት ከመለስ በቀር ሁሉም የቅንጅት 'ስብርባሪዎች' ናቸው የሚል ነው:: ቅንጅት በ97 በቀሰቀሰው የሕዝብ የፖለቲካ ንቃትና በምርጫው ድምቀት አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ የከፈተ ፓርቲ ነው:: መለስ «እንከን የሌለው ምርጫ» እናካሂዳለን ማለቱም አስተዋጽኦ ነበረው:: ቅንጅት በመጨረሻም የምርጫው ውጤት በአስከተለው እልቂትና መፈረካከስ የተጎዳ ፓርቲ ነው:: ስለዚህም ስምምነቱ በማንና በማን መሐከል ተደረገ የሚለው ጥያቄ በቅድሚያ ያልታሰበበትና በግልጽም፣ በስውርም የሚጭረውን ቁስል ያላገናዘበ ነው:: የቅንጅት 'ስብርባሪዎች' ብቻ የተፈለጉበት ምክንያት ምንድን ነው? እነሱስ ብቻቸውን የገቡበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ስምምነቱ በመንግስትና በፓርቲዎች መሐከል ነው? ወይስ በፓርቲዎች? ለሚለው ጥያቄ ግልጽ መልስ ያለ አይመስለኝም:: ምክንያቱም በስምምነቱ ውስጥ የተካተቱት እንደፖሊስ፣ እንደ ደህንነትና እንደአስተዳደር፣ እንደፍርድ ቤቶች፣ እንደመንግስት ንብረት ያሉ ጉዳዮች መንግስት ራሱ የሚፈጽማቸው እንጂ በአገዛዙ ውስጥ የሌሉበት ፓርቲዎችን የሚመለከት አይደለም:: በቅን መንፈስ መሥራት ከተፈለገ መንግስት በራሱ ማስተካከል ያለበትን ሁሉ ሕግ አውጥቶ ከአስተካከለ በኋላ ስምምነት ቢደረግ የተሻለ ይሆን ነበር ብዬ እገምታለሁ:: ለዚህም ቢሆን ምናልባት በቅድሚያ ሁሉም ፓርቲዎች ያሉበት ምክንያት ያስፈልግ ነበር ይሆናል:: አሁን የተደረገው ግን ሦስት የውክልናቸው መጠን ያልታወቀ ቡድኖችና መንግስት ሌሎች ትልልቅ የፖለቲካ ቡድኖችን አግልለው የተስማሙበትን ሰነድ ሌሎቹንም የሚገዛ ሕግ ለማድረግ ነው፤ ይህ ሕግ ሲሆን በጉልበት የሚጫን እንጂ በመንፈሳዊ መሠረት ላይ የቆመና ተቀባይነትን የሚያገኝ ላይሆን ይችላል፤ እንዲህ ከሆነ ትርፉ ምንድን ነው?
3. አቶ መለስ «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» ካለ አሥራ ስምንት ዓመታት ተቆጠሩ:: ዛሬም ከአሥራ ስምንት ዓመታት ትምህርት በኋላ ከስምምነቱ የተገለሉትን የፖለቲካ ቡድኖች እንደተለመደው «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» ማለቱ አይሆንም ወይ? እኔ ያልኳችሁን ካልተቀበላችሁ እኔ የምፈልገውን ሕግ አድርጌ አስገድዳችኋለሁ በሚል ዘዴ መጠቀም የሚያመለክተው ጉልበትን ነው ወይስ ፖለቲካን? ለእኔ እንደሚገባኝ ፖለቲካ ጉልበትን ከትግል መስክ ማስወጣት ነው:: ለእኔ እንደሚገባኝ ፖለቲካ የውይይት፣ የክርክርና የንግግርን አድማስ በማስፋት መቀራረብ፣ መግባባት፣ መቻቻልና ለአገርና ለወገን ዓላማ አብሮ መቆም ነው:: ዓላማው ለአገርና ለወገን ከሆነ በዘዴ ወይም በታክቲክ መለያየቱ የዓላማን አንድነት ሊያደበዝዘው አይገባም:: ዛሬም እንደትናንቱ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁን የፖለቲካ መመሪያ ማድረግ ለማንም አይበጅም:: ስለዚህም የቀሩትንም ተቀናቃኝ የፖለቲካ ቡድኖች ማወያየትና ማግባባት የፖለቲካ ግዴታ ይሆናል:: አለዚያ እነዚህን ሦስት ቡድኖች ተቀናቃኝ የፖለቲካ ቡድኖችን ሁሉ የሚወክሉ አስመስሎ ሕግን የፖለቲካ መሣሪያ ለማድረግ ከተለመደው የችግር መንገድ

አንወጣም ማለት ነው:: ቆራጥ እርምጃ ለመውሰድና የፖለቲካውን ትግል መልክ ለመለወጥ ወኔ ያስፈልጋል፤ ከመለስ ዜናዊ የሚጠበቀው ይህ ነው::

የመፈራረሙ ሥርዓት ያተኮረው በኢ/ር ኃይሉና በአቶ መለስ ላይ ነበር:: ምክንያትም ነበረው:: በመጀመርያ በአለፉት ዓመታት በጎሣና በጥላቻ ፖለቲካ ሁለት ሰዎች የነበራቸው የስሜት አስተዋጽኦ ቀላል አልነበረም:: ስለዚህ በዚህ የመፈራረም ሥርዓት ላይ ጥርሳቸውን እያሳዩ ፎቶግራፍ መነሳታቸው አንድ እርምጃ ወደፊት መሄዳቸውን የሚያመለክት መስሎ ታይቶኛል:: ይቺ አንድ እርምጃ መተማመንንና መግባባትን በመፍጠር በር የምትከፍት ከሆነ ውጤቱ ቀላል አይሆንም:: በዚህ ጉዳይ ላይ ያለምንም ጥርጥር ኃይሉ ሻውል የፖለቲካ ብልህነቱ በጣም ወደታች ቢወርድም ከመለስ የበለጠ መንፈሳዊ ወኔን አሳይቷል:: መለስ ያው ከተለመደው ብልጠት በቀር መንፈሳዊ ወኔ አሳየ ለማለት አይቻልም:: ደካሞችን መርጦ በመሐከላቸው በመቆም የመንፈስ ትልቅነት አይገኝም:: በተጨማሪም መለስን ምንም ዋጋ የሚያስከፍለው ነገር የለም:: ኃይሉ ግን ተጨባጭ ውጤት ካላስገኘ ዋጋ ይከፍልበታል:: መለስ የፖለቲካ ብልህነትና መንፈሳዊ ወኔን ለማሳየት የሚችለው በእኩልነት ከሚጋፈጡት ሰዎች ጋር ተቀምጦና ተወያይቶ ስምምነት ላይ ሲደርስ ነው:: ያኔም ቢሆን መለስ የሚያጣው ወይም የሚከፍለው ዋጋ አይኖርም::- ትርፉ ግን ከፍተኛ ይሆንለታል::

የተለያዩ አመለካከቶች ያላቸውን ሰዎች በኢትዮጵያ ዜና ማሰራጫዎች ማየትና መስማት ያቆምነው በወያኔ ዘመን ነው:: በጣም የሚገርመው ደግሞ ፖለቲካ የተጀመረው በዚሁ ዘመን መሆኑ ነው:: ፓለቲካና የፖለቲካ ፓርቲዎች ባልነበሩበት በአፄ ኃይለ ስላሴም ሆነ በደርግ ዘመን በኢትዮጵያ ራድዮም ሆነ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ነፃ ውይይት ሲደረግ እንደነበረ አንዳንድ ዛሬም እዚያው ያሉ ሰዎች የሚመሰክሩት ነው:: የየፓርቲዎቹ ወኪሎች ሁሉ ተሰብስበው ቢወያዩና እኛም ብንሰማቸው ምን የሚያስፈራ ነገር አለ? መግባባት እንዲዳብርና መተማመን እንዲጠነክር አዳዲስ መንገዶችን መሞከር የሚያስፈልግ ይመስለኛል:: እንዘጭ! እንቦጭ! እያልን የትም አንደርስም::

# መጣጥፎች

# «ኢህአዴግ አዳዲስ የህዝብ ግንኙነት ባለሞያዎችን አስፈረመ!»

## «ተባለ! ... ተባለንዴ!?»

**አቤ ቶኪቻው**

**abeto2007@yaoo.com**

ወዳጄ እንዴት ሰንብተዋል? ግራ ቀኙ እንደምን ውሎ አደረ? ሁሉ አማን ሁሉ ሰላም ይሆን ዘንድ ከመመኘት እና ከመፀለይ የማልቦዝን እኔ ወዳጅዎ ለእርስዎ እና ለሃገሬ ሰላም እንዲበዛ ቀን ተሌት በፀሎት፤ እንዲሁም ለእኔ እና ለቤተሰቤ ቀለብ እንዲገዛ ቀን ተሌት በስራ እየተጋሁልዎ እገኛለሁኝ:: እርስዎም ለእኔ ጤና እና ሰላም በፀሎትዎ እየተጉልኝ እንደሆነ አይጠረጠርም:: በእርስዎ ፀሎት ጤናዬ ባይጠበቅ ኖሮ እንደምናያቸው እንደምንሰማቸው ነገሮች ቢሆንማ ይሄን ግዜ «ማቶ» አልሆንም ብለው ነው?

ወዳጄ የዛሬ ርዕሳችንን ልብ ብለው አይተውልኛል? «ኢህአዴግ አዳዲስ የህዝብ ግንኙነት ባለሞያዎችን አስፈረመ» (አሁን አሁንማ ፖለቲካውን የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ አስመሰሉት እኮ!) ለመሆኑ ይህንን ከንቱ ንግግር ማን ተናገረ? አሉባልተኞች:: አሉባልተኞቹ አዳዲስ የህዝብ ግንኙነት ባለሞያዎች የሚሉት እነማንን ነው? ሶስት የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን:: ለአሉባልተኞቹ እኛ ቅን አሳቢዎች (ነጠላ ሰረዝ) ሶስተኛ አማራጮች (ነጠላ ሰረዝ) ለኢትዮጵያ ህዝብ ስንል ከሰይጣንም ጋር ቢሆን የምንደራደር መለኞች ምን መለስንላቸው «ተባለ!... ተባለንዴ!?» አልናቸዋ! ይህ ጉዳይ ወደ ኋላ ላይ እንመለስበታለን::

እኔ የምለው «ታሪካዊውን» የምርጫ ስነምግባር ደንብ እንዴት ተመለከቱት? አንዳንዶች «ምርጫ ቦርድ ገና በጠዋቱ ብኩርናውን ለኢህአዴግ እና ለአጋር ፓርቲዎች ሰጠ::» እያሉ አስተያየታቸውን እየሰጡ ነው:: (ማስተካከያ «ለአጋር ፓርቲዎች» ተብሎ የተፃፈው በስህተት ስለሆነ ለአገር ፓርቲዎች ሰጠ:: ተብሎ ይነበብ ዘንድ እጠይቃለሁኝ:: እንጂማ የስነምግባር ደንቡን ካወጡት ውስጥ አጋር ፓርቲዎች የታሉ? ኢዴፓም ኢዴፓ ነው፣ ቅንጅትም ቅንጅት ነው፣ (አንዳንድ ወዳጆቼ የቱ ቅንጅት? ብላችሁ ልትጠይቁ እንደምትችሉ ይጠረጠራል:: የእናንተን ቅንጅት አላልኩም ይሄ ሌላ የእናንተ ሌላ::) መኢአድም ቢሆን ገና ለገና ዛሬ «ከቤተኛ» ፓርቲዎች ጋር ሆኖ መከረና «አጋር!» የሚል ስያሜ እንዴት ይሰጠዋል? የለም የአገር ፓርቲ ነው:: እናም «ምርጫ ቦርድ ለአጋር ፓርቲዎች ብኩርናውን ሰጠ» የሚለው ለአገር ፓርቲዎች ተብሎ መነበብ ይገባዋል::)

መቼም አስተያየት አይከለከልምና ሰዎቹ ያሻቸውን አስተያየት ሲሰጡ እኛም «አህ...» እያልን እየሰማናቸው ነው:: የዛሬ ሰው ታድያ እንኳንስ «እህ...» ብለው ሰምተውት ቀርቶ ፊት ነስተውትም መቀጠሉ አይቀርም እና አስተያየት ሰጪዎቹ ቀጠሉ:: «ምርጫ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር አምስት መቶ ምናምን (ቁጥር ላይ እስከዚህም ነኝ የገንዘብ ቁጥር እንጂ የአዋጅ ቁጥር መሸምደድ አይሆንልኝም:: እና ይቅርታ እጠይቃለሁኝ) የሆነ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር ምናምን የተሰጠውን የምርጫ ስነምግባር ደንብ የማውጣት ስልጣኑን ገና የምርጫ ወፍ ሳይጮህ ተቀማ» እያሉ እያሙት ነው::

እንደተሰማው ከሆነማ ምርጫ ቦርድ «ወሬኛም ያውራ ሃሜት ይደርድር እኛስ ሆነናል ፍቅር በፍቅር» የሚለውን ዘፈን ጋብዟቸዋል አሉ:: ዘፈኑ ሲተነተን «ብኩርናዬንም ሆነ ስልጣኔን ማንም የነጠቀኝ የለም ፓርቲዎቹ በስራ እያገዙኝ ነው የቀና ገና ብዙ ያወራል» የሚል ትርጓሜ እንዳለው የዘፈን ግብዣን በመተርጎም አንቱ የተባሉ ባለሞያዎች እያብራሩ ነው:: ምንም እንኳ

ምርጫ ቦርድ ይህንን ቢልም አስተያየት ሰጪዎቹ ግን በትዝታ ወደኋላ ይወስዱናል እኛም መቼም አስተያየት አልሰማም አይባልም ብለን ትዝታቸውን እንሰማለን::

**ትዝታ**

«ያኔም» አሉ አስተያየት ሰጪዎቹ በትዝታ «ያኔም በዘጠና ሰባቱ ምርጫ ጊዜ ምርጫ ቦርድ ቁጭ ብሎ የምርጫውን ውጤት ይፋ ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነበሩ:: እንዲህም አሉ «ኢህአዴግ መንግስት ለመመስረት የሚያበቃውን ድምፅ አግኝቷል:: መላው ደጋፊዎቻችን እና አባላት እንኳን ደስ አላችሁ:: ጣቷን ያላችሁ ደግሞ ከዚህ በኋላ ጣት መቀሰር እንደማይቻል አውቃችሁ ጣታችሁን ትሰበስቡ ዘንድ ትጠየቃላችሁ...» ብለው ለአንዱ የደስታ ለሌላው የማስጠንቀቂያ ንግግር አድርገዋል» አሉ:: «እከሌ አሸንፈሃል ደስ ይበልህ እንቶኔ ተሸንፈሃል አይዞህ የማለቱ ስራ ግን የምርጫ ቦርድ ነበር::» ይላሉ::

«ዛሬም ይኸው ገና በጠዋቱ ምርጫ ቦርድ ሚናውን ተነጠቀ:: በዚሁ ከቀጠለ እና የምርጫ ቦርዱን ስራ ሁሉ ኢህአዴግ እና ቤተዘመድ የሆኑ ፓርቲዎች የሚሰሩለት ከሆነ የልማቱን እንቅስቃሴዎች ማን ሊሰራልን ነው??? ምርጫ ቦርዱስ ምን ሊሰራልን ነው???» እያሉ የጥያቄ መዓት ይደረድራሉ:: እነዚህ ድርድሩን ትተው ጥያቄ የሚደረድሩ ሰዎች እና ፓርቲዎች «ታሪካዊውን» የመጨባበጥ ስርአት ሁሉ «እርስ በርስ ከመጨባበጥ ከሌሎች ጋር መደማመጥ» እያሉ ይተቻሉ::

እልቅስ ወዳጄ እርስዎ ጭብብጦሹን እንዴት ተመለከቱት? ድሮ ድሮ ቦክስ የሚጨባባጡ ሰዎች ዛሬ ዛሬ ለሰላምታ መጨባበጣቸው «ታሪካዊ!» ካልሆነ ሌላ ምን ታሪካዊ ነገር ይገኛል!? በነገራችን ላይ ኢንጂረን ሃይሉ እና አቶ መለስ ተጨባብጠው የተነሱትን ፎቶግራፍ በየትኛውም ድረገፅ ላይ መጠቀም እንደማይቻል ልጃቸው ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ተሰምቷል:: እንዲህ ነው እንጂ! ጎረምሳ ልጅ ያደረሰ እኮ አይደፈርም ጎበዝ! ጥሩ ማስጠንቀቂያ ነው:: ምንም እንኳ አንዳንዶች «ልጁ የአባቱን እና የጠቅላይ ሚኒስትሩን ፎቶግራፍ በፖስት ካርድ መልክ ለማሳተም ፈልጎ ነው:: መቼም ንግድ ከቤቱ ነው!» እያሉ ሊያሽሟጥጡ ቢሞክሩም ማስጠንቀቂያው ግን በእውነት ከአንድ ጎረምሳ የሚጠበቅ «ታሪካዊ» ማስጠንቀቂያ ነው:: እናም በበኩሌ «ሰውየው እንደርሳቸው ጀግና ወልደዋልና የልጁን ስም አንተነህ ብዬዋለው» ብዬ ለአንድ ወዳጄ ባወጋው «ወይ መገጣጠም ስሙም እንዲሁ ነው» አለኝ:: እንዲህ ከሆነ ስምን መላዕክ አወጣው ማለት ነው:: (አንዳንዶች የመላዕክት ስራ ሳይሰሩ ስምን መላዕክ ቢያወጣው ምን ዋጋ አለው ትሉ ይሆናል:: ያሻችሁን በሉ:: ልጁ ግን ቁርጥ አባቱን ሆኖብኛል!)

ሆነም ቀረም ኢንጅረን ሃይሉ (ምነካኝ ኢንጂነር ማለቴ ኢንጅረን አልኩሳ በኦሮምኛ ቋንቋ «ኢንጅረን» ማለት «የሉም» ማለት ነው:: ታድያ አንዳንድ ክፉ አሳቢዎች «ሰውየውን እንጅረን ያለው፤ ሆነ ብሎ «እያሉ የሌሉ» ሊላቸው ፈልጎ ነው::» ብለው እንዳይተረጉሙት ስጋት አለኝ:: እና እኒጅረን ሃይሉ ሳይሆን ኢንጅረን ሃይሉ ይባልልኝ:: ኤድያ በአግባቡ መጥራቱ አሁንም አልሆነልኝም መሰል ምነው በአማርኛው መሃንዲስ ሃይሉ ሻወል ብላቸውስ!) እና መሃንዲሱ እና ጠቅላይ ሚኒስትራችን በረቀቀው «ታሪካዊ» የምርጫ ስነምግባር ደንብ ላይ «ታሪካዊ» ጭብብጦሽ ተጨባብጠዋል:: በነገራችን ላይ ይህ የስነምግባር ደንብ በርካታ መልካም ሃሳቦችን የያዘ መሆኑ

አይካድም፡፡ ለምሳሌ «ጋዜጠኞች ፓርቲዎችን ይጠይቁ ዘንድ አትከልክሏቸው» የሚለው አንዱ የምርጫ ደንቡ አካል መሆኑ ከሚያስመሰግኑት አንዱ ነው፡፡ ይህንን ለአንድ ወዳጄ በነገርኩት ጊዜ «ሞኝ አትሁን» አለኝ፡፡ እንዴት? አልኩት «ሌሎቹን ተዋቸው ሽማግሌው በደከመ አቅማቸው እጃቸው እስኪርገፈገፍ እየተጨባበጡ ያፀደቁትን ደንብ ረስተው አየል ያሉት በየፍርድ ቤቱ ጋዜጠኞችን በመክሰስ ተጠምደው በየት በኩል ጋዜጠኞች ወደ ፓርቲዎች ይሔዳሉ?» አለኝ፡፡ አውነት ግን ቢያንስ ድርድሩ ላይ ዋና የነበሩ ዋና ሰዎች ጋዜጠኞችን አሁንም ድረስ እየከሰሱ መሆኑ ሲሰማ ከውጪ ላለ ሰው በስነምግባር ደንቡ ላይ «ጋዜጠኞች ለጥያቄ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው! ከመጡ በኋላ ባይሆን ፍርድ ቤት ገትሯቸው» ተብሎ ተፅፏል እንዴ? ያሰኛል፡፡ እና እባካችሁን አታስፎግሩን!

ወደቀደመው ወጋችን ስንመለስ ሰዉ እንዳይሆን እንዳይሆን ሰዎቻችንን እያብጠለጠለ ነው፡፡ አልፎ ተርፎ በየጋዜጣው እየሰጡ ያሉትን ቃለ ምልልስ እየመዘዙ እንዴት እንዲህ ይባለል እተባለ ነው፡፡ እኛስ ማን አለብን «ተባለ ተባለንዴ!?» እያልን እየመለስንላቸው ነው፡፡ አሁንለታ አንዱ - መሃንዲሱ በአንድ ጋዜጣ ላይ የሰጡትን አስተያየት እያስነበበኝ «በሌሎች ሀገሮች ሰዉ ስንት ደም ተቃብቶ ይጨባበጣል እኛ ትንሽ ነው የተኳረፍነው፡፡» ብለው የተናገሩትን እያስነበበኝ «እኒህ ሽማግሌ እርጅናው ተጫጭኗቸው ትንሽ እና ትልቅ መለየት አቃታቸው እንዴ የሞተው ሰው ቁጥር እኮ...» ብሎ የአንድ ቤት ሰራተኛ ደሞዝ የሚያኽል ቁጥር ነገረኝ፡፡ (በነገራችን ላይ የቤት ሰራተኛ ደሞዝ በጣም ጨምሯል፡፡)

ሌሎችም ተደራዳሪዎቹ እንዲሁ በየጋዜጣው እየሰጡ ያለውን አስተያየት እና በቴሌቪዥን እያደረጉ ያለውን ዲስኩር እየሰሙ «ሰዎቹ ለኢህአዴግ ቅስቀሳ እና ፕሮፖጋንዳ ስራ ለመስራት ነው የፈረሙት ወይስ የምርጫ ደንቡ ላይ ነው የፈረሙት» ሲሉ እያሾሞሩ ነው፡፡ ታድያ እኛም «ተባለንዴ!?» ብለን አፀፋውን መልሰናል፡፡ አንዱ ወዳጄ - «ሁለቱስ እሺ ቀድሞውኑም የራሳቸውን ማሊያ ለብሰው ለኢህአዴግ ሊጫወቱ ከፈረሙ ቆይተዋል እኒህ አዲሱ ፈራሚ ግን ምናለ ፊርማቸው እንኳ እስኪደርቅ ቢጠብቁ ፕሮፖጋንዳውን አበዙት እኮ!» አለኝ፡፡ ሌላ ምንም መልስ አልነበረኝም እና «ተባለ!... ተባለንዴ!?» ብዬ ሽሙጡን በሽሙጥ መልሼለታለሁኝ «ከኛ በላይ ማሽሟጠጥ...» የሚለውንም ተረት ጋብዤዋለሁኝ፡፡

ወዳጄ የሆነ ሆኖ ነገሩ አንድ ጋዜጣ እንዳለው «ጨዋታው ተጀመረ!» ያስብላል፡፡ ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ድርድሩም ሆነ ውድድሩ መልካም ፍፃሜ እንዲኖረው በፀሎት መትጋት ያስፈልጋል፡፡ እኔ እተጋለሁ እርስዎስ!?

**በመጨረሻም:**

ክበበው ገዳ ባለፈው ጊዜ ካሳተማቸው ጨዋታዎች ሁሉ አንጀቴን የበላችኝ «ጋሽ ፖሊሱ» የምትለው ዘፈን ነች፡፡ በጋሽ ፖሊሱ ዘፈን ላይ ያሉ ነጋዴዎችን አራት ኪሎ ፒያሳ አውቶቢስ ተራ በአጠቃላይ ሁሉም ቦታ አሉ፡፡ ታታሪነታቸው የሚደንቅ ነው፡፡ በርግጥ እኒህ ታታሪዎች ትትርናቸውን እያሳዩ ያሉበት መንገድ (የጎዳና ንግድ) እውነትም የሚበረታታ አለመሆኑ ርግጥ ነው፡፡ ነገር ግን ደንብ አስከባሪዎቹ የሚያደርጉባቸው ጭንኔ ወደ ሌላ ምሬት የሚከት ነው፡፡ (ደግነቱ ብሔራዊ ውትድርና የለም፡፡ እንጂ ወዶ ገብ ያስገባል፡፡)

ሰሞኑን በአራት ኪሎ ጎዳና ሳልፍ እነዚህ «ጋሽ ፖሊሱ» የተዘፈነላቸው «ህገወጦች ይከለከሉበት የነበረው ቦታ ላይ ድንኳን ተጥሎ አየሁኝ «እነዚህ ሰዎች ብለው ብለው መንገዱን ቤታቸው አድርገውት ሰርግ እየደገሱበት ነው እንዴ? ብዬ እያሰብኩኝ ወደ ድንኳኑ ቀረብኩኝ ይበልጥ ወደ ድንኳኑ ስቀርብ ግን ድግሱ «የህገወጥ» ነጋዴዎቹ አይደለም:: «ህጋዊ» የቀበሌ ሰዎች የደገሱት ድግስ ነው:: ከ እስከ የ የሚል ቀን የተለጠፈበት ድንኳን ለእግረኛው «የማሪያም መንገድ» እንኳን ሳይተው ንግዱ እየጦፈ ነው::

## <u>ጥያቄ</u>

ዛሬ የቀበሌ ጥቃቅንና አነስተኛ ነጋዴዎች በድንኳን እየነገዱበት ያለው ቦታ ትላንት ሌሎች ያለ ድንኳን ሲነግዱ «ህገ ወጥ» የተባሉበት ነው:: ታዲያ እኒህ ነጋዴዎች ድን ኳን ጥለው ሲነግዱ ዝም የተባሉት በቀበሌ ስለታቀፉ ነው? ወይስ በድንኳን ስለታቀፉ?

**አማን ያሰንብተን**

# የመድረክ አባል ድርጅቶች ጥምረትና ነባራዊው ሁኔታ

**በታምራት ታረቀኝ**

የአብሮ መስራትን ጠቀሜታ የማይናገር ፖለቲከኛ የለም:: ምርጫ በተካሄደ ማግስትም የተሸነፍነው ራስ በራሳችን በመወዳደራችን ነው በማለት ቁጭት መሰል ቃል ከፖለቲከኞች አንደበት መስማት የተለመደ ነው::ከዚህ አልፎም ኢህአዴግ የሚገዛው በራሱ ጥንካሬ ሳይሆን በእኛ ድክመት ነው በማለት ደፍረው በአደባባይ ሲናገሩም አዳምጠናል፤ አንብበናል:: ነገር ግን ምክንያቱን መርምሮ የጋራ እና የተናጠል ድክመትን ፈትሾ በድፍረት የሚነገረውን ቃል ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል ቁርጠኝነት አይታይምና ዛሬም በትናንቱ መንገድ መጓዙ ነው የተመረጠው::

ምርጫ በሩጫ እንደማይሳካ በጡንቻም የህዝብን አመኔታ እንደማያስገኝ እየታወቀ ተቀዋሚ ፓርቲዎች ጥምረት፣ ትብብር፣ ቅንጅት፣ወዘተ በማለት መሯሯጥ የሚጀምሩት የምርጫ ነፋስ መንፈስ ሲጀምር ነው፡፤ይህ ደግሞ ነገረ ሥራውን ሁሉ «የእነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ »እንደሚባለው ያደርገዋል::

በአንፃሩ ገዢው ፓርቲ የሚያከናውናቸው ተግባራት ሁሉ የሚያመላክቱት ከምርጫ 97 የተማረ መሆኑን ነው:: ምርጫ በጡጫ ያስከተለውን ችግር ለመመርመር ጊዜ አልፈጀም:: የምርጫው ውጤት ገና ሳይጠናቀቅ እሱ ወደ ግምገማ ነው የገባው::እናም አሁን የምርጫ 2002 ዝግጅቱን ያጠናቀቀበት ደረጃ ላይ ይገኛል::

ተቀዋሚዎች ግን ስለ ምርጫው ምን ዝግጅት እንዳላቸው በተግባር የሚታይ ቀርቶ ምን እያሰቡ እንደሆነ እንኳን የሚገልፁት ነገር አልሰማንም:: ቅንጅት በስድስት ወር ዝግጅት በምርጫ ተወዳድሮ ውጤት ማምጣቱን እያሰቡ በዚህ ራሳቸውን የሚደልሉ ካሉ ፖለቲከኛነታቸው አጠራጣሪ ነው:: ፖለቲከኛ ዛሬን ከትናንት እያነፃፀረ እና ዛሬ ላይ ሆኖ ነገን እየተነበየ የሚጓዝ መሆን አለበት:: ቅንጅት በስድስት ወር የፈጠረው የህዝብ ተነሳሽነት ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ዕውን ይሆናል ብሎ ማሰብ ምርጫ 97 በህዝቡ ላይ ያደረሰውንና ተቀዋሚዎችም የፈፀሙትን ህዝቡን ያስከፋ ተግባር ለመርሳት መቃጣትና እሁን በገገርው ፓርቲ እየተፈፀሙ ያሉ ጉዳዮችን አለማጤን ይሆናል::

ወቅታዊውን የመተባበር ሀሳብ እያነሱ ያሉት «መድረክ»በሚል መጠሪያ የተሰባሰቡት ፓርቲዎች ቅንጅት ፌዋረናል የጋራ መንግስት ለመመስረትም ተስማምተናል ቢሉም በመከከለቸው ያለውን መሰረታው የዓላማ ልዩነት እንዴት እንደሚያስታርቁት አልነገሩንም:: ዛሬ መፍትሄ ያልተገኘላቸውና በልዩነት ተመዝግበዋል የሚባሉ ልዩነቶች ቤተ መንግስት ሲገባ መፍትሄ ያገኛሉ ማለት ከፖለቲከኞቻችን ባሕርይ አንጻር የማይታመን ነው:: በመድረኩ ፕሮግራም መሰረት እንቀጥላለን ከተባለ ደግሞ የአንድነት ዓላማና መርሆዎች ሙሉ በሙሉ ይጠፋሉ ::

## መቀናጀት ምንድን ነው?

መቀናጀትን ከከተሜው ይልቅ የገጠሩ ነዋሪ በሚገባ ያውቀዋል::ይፈፅመዋልም::«አንድ ሰው አስቦ አንድ በሬ ስቦ» አይሆንምና አንድ በሬ ብቻ ያላቸው አርሶ አደሮች የእርሻ ጊዜ ከመድረሱ በፊት መቀናጆ ይፈልጋሉ ያፈላልጋሉ:: ከበሬም አባያና ትጉ፣ሰነፍና ብርቱ አለና ከበሬያቸው ጋር ተስማምቶ ርሻቸውን በወቅቱና በተገቢው ማከናወን የሚያስችላቸውን በሬ ካለፈው ዓመት የእርሻ ወቅት አስተራረሱ ያጠናሉ የባለቤቶቹ ፍቅር ሳይሆን የበሬዎቹ መጣጣም መቻል ነውና ዋናው ተፈላጊ የእርሻ ወቅት ከመድረሱ በፊት ውል አስረው ስምምነት ፈፅመው ዝግጅታቸውን ያጠናቅቃሉ::ይህ ሁሉ ሆኖ ወቅቱ ደርሶ በሬዎቹ ተቀናጅተው በተግባር ሲፈተኑ ሊጣጣሙ ካልቻሉ በሂደትም ተግባብተው ሞፈሩን የሚስቡ ካልሆኑ ይበልጡኑ አንዱ አባያ ከሆነ የሌላኛው በሬ ባለቤት የእርሻ ወቅት ከማለፉ በፊት ሌላ መቀናጆ ፍለጋ ይገባል:: የመቀናጆ በሬ ቀለቡ በየባለቤቱ፣ አዳሩ በየቤቱ፣ ሲያርስ ለሁለት ጌቶች ነው::

የፓርቲዎች መቀናጀትም ከዚህ መሰረተ ሀሳብ ብዙ የሚርቅ አይደለም::የመሪዎች ፍቅር ሳይሆን የፓርቲዎች ዓላማ ነው ወሳኙ:: የሚቀናጁበት መርህ ግልጽ ሆኖ መታወቁ ነው መሰረቱ:: እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሚሰሩ የሚፈጽሙት ውል ነው ማሰሪያው:: ለአደባባይ ቢበቃ ፍላጎታችንን ከወዲሁ ያመክንብናል የሚሉትን ጉዳይ እያለባበሱ በየወንዙ እየተማማሉ ከዳገቱ ግርጌ ሳይደርሱ እየተሰነካከሉ መውደቅ ለሐገራችን ፓርቲዎች ዋንኛ መታወቂያቸው ሆኗል:: ዛሬም በትናንቱ መንገድ መሄድን የመረጡ ወገኖች ጩኸታችን ከትናንት ስጋት የመነጨ፣ማሳሰቢያችን የትናንቱ ዛሬ እንዳይደገም ከመስጋት የመጣ መሆኑን እያወቁ ፣አብሮ መስራትን የማንፈልግ እንደውም «ፀረ ሕብረት» እንደሆንን አድርገው ሊፈርጁን ይዳዳቸዋል:: ለእነዚህ መልሳችን አጭር ነው::ትናንትን ማስታወስ የማይፈልጉ ያንኑ ስህተት ለመድገም የተዘጋጁ ናቸው የሚል::

## የአንድነትና የመድረክ ግንኙነት ተለዋዋጭ ገፅታ

የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ዓዋጅ ቁጥር 573/2000 «ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ፓርቲዎች መዋሀድ፣ ግንባር መፍጠር መቀናጀት እንደሚችሉ ይገልፅና እያንዳንዱ እንዴት በማንና ለምን እንደሚፈጸም የዘረዝራል:: ስለ መቀናጀት የሚገልፀው አንቀፅ 35(1) «በዚህ አዋጅ መሰረት የተመዘገቡ ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለተወሰነ ጊዜና በተወሰኑ ጉዳዮች ዙሪያ ተቀናጅተው እንደ ሁኔታው በሀገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ» ይላል:: አንድነት ከመድረክ ጋር ግንኙነት እንዲጀምር ሲታሰብ እነዚህን ጉዳዮች ሊያሟላ የሚያስችል ጅማሮ ነበር:: ጅማሮው በአጭር ተቀጭቶ በድንገት «ከዛሬ ጀምሮ መቀላቀል አለብን» መባሉ ነው ከትናንት የአብሮነት ጉዞ መደነቃቀፍ ልምዳችን ላይ አዲስ ስጋት ፈጥሮብን አጥብቀን እንድንጮህ የሚያደርገን:: አዋጁ እንደሚያመለክተው መድረክ ውስጥ የተሰባሰቡ ፓርቲዎች (የግለሰቦቹ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ) ለምንና እንዴት እንደሚቀናጁ ግልጽ አድርገው መነሳት ያስፈልጋቸዋል:: አለበለዚያ የተለመደው በየወንዙ እየተማማሉ በየዳገቱ መከዳዳት ይቀጥላል:: በቅርቡ የሚሰማው አንድነት አማራውን ይወክላል የሚባለው የድብብቆሹ ጨዋታ ይፋ መሆን ጅማሮ ይመስላል::

## አንድነት ከመድረክ ጋር ለመቀላቀል የሄደባቸው መንገዶች:

ሀ- መድረክ ራሱን ለማስተዋወቅ በጠራው ጋዜጣዊ ጉባኤ ላይ እንዲገኝ አንድነት መጋበዙ በተገለጸበት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ሊቀመንበር ብርቱካን «ከመድረኩ አብሮ የመስራት ጥያቄ የቀረበው ቀደም ብሎ እንደነበረ ነገር ግን በወቅቱ የነበረው አስተባባሪ ግብረ ኃይል ጥያቄውን ማየት የማይችል በመሆኑ፣አንድነት ከተመሰረተም በኋላ ህጋዊ ምዝገባውን ባለማጠናቀቁ ምክንያት ለመድረኩ ጥያቄ ምላሽ ያለመሰጠቱን» አስረዳች:: ተሰብሳቢውም በዚህ ሁኔታ በሊቀመንበር የሚመራ ቡድን መላክ ተገቢ እንዳልሆነ በመገንዘብ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም የውጪ ግንኙነት ኃላፊ ስለሆኑና ከመድረኩ ጋርም ግንኙነት እንዳላቸው ስለተገለፀ እሳቸው ተወክለው በመድረክ ጋዜጣዊ ጉባዔ ላይ እንዲገኙ ወሰነ::

ለ- ለሁለተኛ ጊዜ የመድረክ ጉዳይ በአጀንዳነት የቀረበው በ 29/03/2001 ዓም የስራ አስፈፃሚው ስባሰባ ላይ ነበር:: «የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰላለፍ እና የትብብር ጥያቄ» በሚል ርዕስ የጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ ያዘጋጀው ሰነድ ከመድረክ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ለመወሰን ይረዳል ተብሎ ቀደም ተደርጎ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላቱ ታድሎ የነበረ በመሆኑ አንዳንዶቹ ከሰነዱ ውስጥ «የመድረክ አባል መሆን» የሚለውን ብቻ ለይተን ከአጀንዳው ጋር እንየው ሲሉ ሊሎች ደግሞ «ሰነዱን የፓርቲ አድርጎ መቀበል አይቻልም» በማለት ጭራሹን ሰነዱ መሉ በሙሉ ውድቅ ሊሆን እንደሚገባ ተከራከሩ:: ይህ ሀሳብ ጠንካራ ተቃውሞ አሳነሳ:: አንብበን ከፓርቲው መርህ ጋር ይጋጫል የምንለውን ለይተን ለዚህም በቂ ምክንያት አቅርበን በዝርዝር ሳንወያይበት ውድቅ ይሁን ማለት ለጥናትና ምርምር ሥራ አክብሮት ያለመስጠት ነው ተባለ:: ይህ ውይይት የተቋጨው ሰነዱን መርምረው ሀሳብ የሚያቅርቡ ሶስት ሰዎችን በመመደብ ሲሆን ሶስት የሥራ አስፈፃሚ አባላት ግን ይህን ተቃወሙ:: የተመደቡት ሰዎችም ሰርተው ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አላቀረቡም:: የጠየቃቸውም የለም::

የጥናትና ምርምር ሰነድ ጉዳይ በዚህ ተዘግቶ የመድረኩን ጉዳይ ለብቻ ለማየት ስምምነት ተፈጥሮ ውይይቱ ቀጠለ::በዚህ ውይይት የተነሱ ጥያቄዎችንና የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ማየት

በኃላ የተፈጠረው ጥድፊያ እንዴትና ለምን ሆነ ብሎ ለማጣየቅ ስለሚያስችል ዋና ዋናዎቹን እንመልከት::

- ከፊት ስፊት ያለውን ተራራ በጋራ መግፋት አለብን፣ተራራውን ገፍተን ሜዳውን ካስተካከልን በኃላ እያንዳንዱ ፓርቲ በያዘው ፕሮግራም መሰረት ይጋልባል ነው የሚሉት::

ይህ እንዴት ይሆናል? የውይይት መድረክ ነው ተብሏል ሀገሪቱ ያሉባትን ችግሮች የሚፈታ ነው ወይንስ ስለምርጫ 2002 ብቻ? (ዶ/ር ኃይሉ )

ምክክር መድረክ ተባለ ፣ኢህአዴግን የሚቃወሙ ተባለ፣ ግለሰቦች ተባለ አልተጣጣመልኝም: (ወ/ሮ ላቀች)

ትልቅ ጉዳይ ነው ለእኛ:: በጣም አስበንበት ብንወስን ጥሩ ነው:: በሌላ ቀጠሮ ከእነርሱ ሰው ጋብዘን መጥተው እንዲያስረዱን ብናደርግ:: (ዶ/ር ያዕቆብ)

መረጃዎች ጥቁር ነጭ ሆነው ይምጡ:: የእኛን ቦተም ሳይን ግልጽ እናድርግ:: (አቶ ብሩ)

ፋይናንሻል አሬጅመንቱ እንዴት ነው? ኮንስቲቲወንሲያቸው ምንድን ነው?ዴሞክራሲያዊ ገፅታቸው

እንዴት ነው? (ኢ/ር ግዛቸው)

በኢትዮጵያ አንድነት ሳይ ቁርጥ ያለ አቋም አላቸው ወይ? (ዶ/ር ያዕቆብ)

የመሬት ጉዳይ እንዴት ነው? (አቶ ተመስገን)

መደራደር እንችላለን ወይንስ እነርሱ የተስማሙበትን ተቀብለን አባል መሆን ነው ? (አቶ ታምራት)

የህገ መንግስቱን አቀፅ 8 እንዴት ያዩታል?ሀገሪቱ ራሷን የቻለች ሀገር ናት አይደለችም?ለዚህ ምላሻቸው ምንድን ነው? ዶ/ር ያዕቆብ ፣ይህን ጥያቄ በመድረክ ሲፖዚየም ላይም አቅርበውት ነበር)

የግለሰብ ነፃነት ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ? ጥርት ቢያደርጉልን::(አቶ ብሩ)

በፌዴራሊዝም አወቃቀር ላይ ከቋንቋ ባሻገር ምን አቋም አሳቸው? እዛ ውስጥ ገብተን ሳይሆን መድረክ እና አንድነት ሆነን መተባበር እንችላለን ወይ? (ኢ/ር ግዛቸው)

እነዚህና መሰል ጥያቄዎች ተነስተው ውይይት ከተደረገ በኋላ ሊቀመንበር ብርቱካን መልስና ማብራሪያ ጠይቃ እንድታመጣ ኃላፊነት ተሰጥቶ የመድረኩ መተዳደሪያ ደንብና ይፋ መግለጫዎች ለሥራ አስፈፃሚ አባላቱ ደርሰው እነርሱን በመመርመር ከውሳኔ ላይ ለመድረስ ስምምነት ተደረገ፡፡ አንድነት ከመድረክ ጋር ለመቀላቀል ሲወሰን እነዚህ በሥራ አስፈጻሚው ስብሰባ ላይ የተነሱ ጥቂዎች መልስ አግኝተው፣ በቂ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸው፣የመድረኩ መተዳደሪያ ደንብ ተመርምሮና መግባባት ላይ ተደርሶ ነው ወይ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል:: ቅልቅሉ የተፈፀመው ጥያቄዎቹ መልስ ሳያገኙ ከሆነ ደግሞ መጀመሪያውኑ ለምን ተነሱ የሚል ጥያቄ ያስነሳል:: በተለይ መልስ ሊያገኙ የሚችሉ የማይመስሉ ጥያቄዎችን ያነሱና የመድረክ ሰዎች እኛ ጋር መጥተው ማብራሪያ ሊሰጡን ይገባል ብለው የተከራከሩ ወገኖች ከመቅፅበት ምንም ሳያስፈልግና ምንም ሳይደረግ አንድነት ከመድረክ ጋር መቀላቀል አለበት ብለው የአቋም ለውጥ ማድረጋቸው ጉዳዩን አነጋጋሪ ያደርገዋል::

ብርቱካን በታሰረች በ12ኛ ቀን በ02/05/2001 ዓም በተካሄደው የስራ አስፈፃሚ ስብሰባ የመድረክ ጉዳይ አጀንዳ ሆኖ ቀረበ:: አንዳንድ የስራ አስፈፃሚ አባላት በእለቱ ውሳኔ ለማስወሰን ቆርጠውና ተዘጋጅተው የመጡ መሆናቸው ከንግግራቸው ይታወቅ ነበር:: ሌሎች ደግሞ የጥናትና ምርምርን ሰነድ አይተው ሀሳብ እንዲያመጡ የተመደቡት ሰዎች እስካሁን የተባሉትን አልፈፀሙም፣መተዳደሪያ ደንባቸውን ሳንመረምር እንዴት እንቀላቀል ይባላል? ይህ ሥራ አስፈፃሚ በዚህ ጉዳይ ላይ መወሰን አይችልም::ለምርጫው አንድ ሆነን እንቀርባለን፣ የምርጫ ክልሎችን እንከፋፈላለን፣ ከዛ በኃላ ሁሉም ወደ ነበረበት ይመለሳል የሚባለው እንዴት ይታያል፣በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ስላሉ በርጋታ ልንወያይባቸው ይገባል፣አባል መሆናችንን ካረጋገጥን ጊዜ ጀምሮ የደንቡ ተገዢ ስለምንሆን አጥርተን ማወቅ አለብን:: የሚሉ ጥያቄዎችና አስተያየቶችም ቀረቡ::

በእለቱ አስወስነው ለመውጣት ተዘጋጅተው የቀረቡት ደግሞ ዘገያችሁ የሚል ጥያቄና ነቀፌታ እየቀረበብን ነው::በአባልነት እንግባና ምን ቅርጽ ይኖረዋል የሚለው ወደ ፊት የምንነጋገርበት ይሆናል:: እዛው ሰምጦ መቅረት አይደለም መሳብ ይቻላል፣ገብቶ መውጣትም ይቻላል::የሚሉ ሀሳቦችን ይዘው ተከራከሩ::ደንባቸውን አንብበነው መጥተናል በድምፅ እንወስን የሚል ግፊትም ጀመሩ::

አብሮ መስራትን የተቃወመ የለም ይሄው ይገለፅላቸው:: ገብቶ መውጣትም ይቻላል የሚለው ፈጽሞ መነሳት የሌለበት ነው:: ትብብር የምንጀምረው እስከዳር ድረስ ለመዝለቅ አምነንና ወስነን መሆን አለበት እንጂ ቢሆን ይሆናል ባይሆን አይተነው ይቀራል በሚል ስሜት መሆን የለበትም :: ስለሆነም በቂ ውይይት አድርገን በመካከላችን ለምን መተማመን አንፈጥርም ቢባልም ፈቃደኝነቱ ጠፍቶ በዘጠኝ ድጋፍ በአንድ ተቃውሞና በሦስት ድምፅ ተአቅቦ ተወሰነ:: ሥራ አስፈፃሚው ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ሲወስን ጉዳዩ ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ስለመቅረቡ አልተነጋገረም:: እንደውም ስብሰባው የተበተነው ስክነት በጎደለው መልክ ነበር:: ከዛ በኋላም ቢሆን ስራ አስፈጻሚው ተገናኝቶ ለብ/ም/ቤቱ በሚቀርብበት ሁኔታ ላይ አልተነጋገረም::ዋና ፀሐፊው ግን በ09/05/2001ዓም ለተካሄደው የብሔራዊ ም/ቤ/ት ስብሰባ «በስራ አስፈፃሚ ደረጃ ከመድረክ ጋር ለመስራት ወስነናል» በማለት ም/ቤቱ

እንዲያፀድቅ ጠየቁ።ከብዙ ውይይት በኋላ ሥራ አስፈፃሚው በምን ሥልጣኑ ነው የወሰነው የሚል ጥያቄ ሲነሳ «አልወሰንም የውሳኔ ሀሳብ ነው ያመጣነው »ተባለ። ይህ ስብሰባ የተቋጨው የመድረክ ሰነዶችና የጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ ሰነድ ለም/ቤቱ አባላት እንዲደርስ እና ሰነዶቹን መርምሮ ለመወሰን ቀጠሮ በመያዝ ነበር።

የም/ቤቱ አባላት የደረሳቸውን ሰነድ አንብበው ለውሳኔም ተዘጋጅተው በ30/05/2001 ዓም በተጠራው ስብሰባ ተገኙ።የፓርቲው ዋና ፀኃፊ ግን ሥራ አስፈፃሚው ያልመከረበትና ጭራሹኑ የማያውቀውን «በእጃችሁ የሚገኘው ሰነድ አይሰራም መድረክ የሚባል አካልም የለም፣ እንደገና ከዜሮ ነው የምንጀምረው» በማለት ተናገሩ። ይህን ያዳመጡ የም/ቤት አባላት ለአንድ ወር ያነበቡት ሰነድ አይሰራም መባሉ ቢያስገርማቸውም «አንድነት ከመድረክ ጋር በምን ጉዳይ ለምን ዓላማ አብሮ እንደሚሰራ የሚገልፅ የመግባቢያ ሰነድ ተሰርቶ ይቅረብልን በማለት ለስራ አስፈፃሚው መመሪያ ሰጡ።

## አንድነት ከመድረክ ጋር ተቀላቀለ የሚለው መግለጫ

አንድነት ከመድረክ ጋር መቀላቀሉን ለማወጅ የካቲት 12/2001 ዓም ጋዜጣዊ መግለጫ የመጠራቱ ምስጢር ለአንድነት ብ.ም.ቤት ሰብሳቢ ለዶ/ር ሽመልስ አስቀድመው ያደረሱት ኢ/ር ግዛቸው ነበሩ። ዶ/ር ሽመልስ በወቅቱ ለምክር ቤቱ እንደገለጹት ኢ/ር ግዛቸው ሂደቱን የሚቃወሙ መስለው ዶ/ር ሽመልስ የተቃውሞ ደብዳቤ እንዲጽፉላቸውና እሳቸው ለሥራ አስፈጻሚው አቅርበው እንዲታይ እንደሚያደርጉ በነገሩዋቸው መሰረት ነበር ደብዳቤ የጻፉት። ደብዳቤ ው ከደረሳቸው በኋላ የሥራ አስፈጻሚውን ለ13/06/2001 ስብሰባ ቢጠሩም ደብዳቤውን ከተቃወሙት ሰዎች አንዱ መሆናቸው እስከሁን ያልተገለጸ ምስጢር ነው። አንድነት ከመድረክ ጋር ተቀላቀለ የሚለው መግለጫ ግን በ12/06/2001ዓም በይፋ ተሰጠ። ይህም በፓርቲው ውስጥ ሰፊ ልዩነት ፈጠረ። የልዩነቱ ምክንያት ተቀላቀለ መባሉ አይደለም። ምን ይዛችሁ በምን ተስማምታችሁ ነው የተቀላቀላችሁት ምክር ቤቱስ ይህን መች ወሰነላችሁ ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ገና በመነጋገር ላይ ነን። ተቀላቀልን የሚለው የቃል ትርጉም ጉዳይ ነው የሚል መሆኑ ነበር። መድረክ የሚባል አካል የለም ተብሎ አንድነት ከመድረክ ጋር ተቀላቀለ የሚል መግለጫ ተሰጠ። የመድረክ ሰነድ አይሰራም ተብሎ «አንድነት መስፈርቱን አሟልቶ በመገኘቱ መድረክ ተቀብሎታል» ተብሎ ተገለፀ። በዚህ ሁኔታ የቃላት ጨዋታና ድብብቆሽ የተጀመረ ሂደት ሀገራዊ ለውጥ ለማምጣት ሕዝባዊ ድልም ለማጎናፀፍ መብቃቱ እያጠራጠረን ነው ከጅምሩ አበክረን መጮኻችን።

በ29/03/2001ዓም በወ/ት ብርቱካን በተመራው ስብሰባ ላይ መልስ የማያገኙ የሚመስሉ ጥያቄዎችን ያነሱ ወገኖች የአቋም ለውጥ አድርገው አንድነት ከመድረክ ጋር እንዲቀላቀል ሽንጣቸውን ገትረው ተከራካሪ ሆነው መገኘታቸው ነው ስጋታችን እንዲጨምር ያደረገው። ለውይይት በሚቀርቡ አጀንዳዎች ላይ አስተያየት የሚሰጠውና አቋም የሚያዘው በነገሩ ይዘት ሳይሆን ስብሰባውን በሚመራው ወይንም አጀንዳውን ባቀረበው ሰው ማንነት ላይ በመመስረት ከሆነ ችግራችን ከመሰረቱ የሰፋ መሆኑን የሚያሳይ ይሆናል። ባለፉት 18 ዓመታት ብቻ ብዙ የሕብረት፣ የቅንጅትና የትብብር ጅምሮችን አይተናል።አሁን መድረክ አካባቢ የሚገኙ ፖለቲከኞች የመሯቸውም ሆኑ የተሳተፉባቸው የአብሮ መስራት ጅምሮች እንዳቸውም ለውጤት አለመብቃታቸውን እናውቃለን። ይህ ማለት ግን ትናንት ውጤታማ አልሆኑምና

ዛሬም ሊሆኑ አይቻላቸውም ማለት አይደለም:: ትናንት ዛሬ አይደለምና! ጥያቄ የምናነሳው በአጀማመር ሂደቱም ሆነ በሚታየው ግንኙነት ከትናንት የተሻለ ነገር ያለማየታችን ነው::«ቢሆን ይሆናል ባይሆን አይተነው ይቀራል» የሚለው አስተሳሰብ ዛሬ በደረስንበት ደረጃ ቦታ አይኖረውም:: የአብሮ መስራት ጥንስስ በጥናት ሊጀመር፣በዕቅድ ሊከናወን ውል ማሰሪያ በተበጀለት ሕግ ሊመራ ይገባዋል:: በግለሰቦች መቀራረብ ላይ ሳይሆን በፓርቲዎች ዓላማና ግብ ላይ መመስረት አለበት::የተወሰኑ ሰዎችን ለሥልጣን ማብቃትን ሳይሆን ሀገራዊ ዲሞክራሲ ማስፈንና መሰረታዊ የሥርዓት ለውጥ ማምጣትን ያለመ መሆንም ይኖርበታል:: የመድረኩ ጉባኤ በተከሄደ ማግስት ማብራሪያ በሚል ከአንድነት የወጣው ጽሁፍም ስራው ሁሉ በስክነት ያልተሰራ መሆኑን የሚያሳይ ነው::

## ምርጫን በጋራ ለመወዳደር መጣመር::

የምርጫ መተባበር፤ ገዢውን ፓርቲ ለማሸነፍ ሲሉ ብቻ በምርጫ ዋዜማ የሚፈፅሙት የይድረስ ይድረስ ሥራ መሆን የለበትም::እንዴት? የት እና በምን ሁኔታ ለምርጫ መቅረብ እንደሚቻል ከጅምሩ መስማማት ያስፈልጋል:: ቢያሸንፉ እንደምን የውጤቱ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ከወዲሁ ውል ማሰሪያ ሊያበጁለት ይገባል:: በተለይ ተጣማሪዎቹ ፓርቲዎች የዓላማና የአደረጃጀት ልዩነት ያላቸው ሲሆኑ መንግሥት የመመስረት ዕድሉ ቢገጥማቸው ገቢራዊ የሚያደርጉት ሀገራዊ አጀንዳ ተለይቶ ለመራጩ ሕዝብ ጭምር በቅድሚያ መገለፅ አለበት:: ገዢውን ፓርቲ በመጥላት ብቻ ሳይሆን አላማቸውን ተቀብሎ በአማርጭነታቸው አምኖ የሚመርጣቸው መራጭ ነው ማፍራት የሚኖርባቸው::

ከዓመታት ጉዞአችንና ሳይሳኩ ከቀሩት የአብሮ መስራት ጅምሮች የተገነዘብነው ዋንኛ ችግር የሥልጣን ክፍፍል ጉዳይ ቀድሞ የሚታሰብበትና እልባት ሊደረግበት የሚገባ ነው:: ለመለያየት ዋንኛ ምክንያት መሆኑን በተግባር ያሳየውን ይህን ጉዳይ በይደር አቆይቶ በሌሎች መስማማት ለውጤት አያደርስም ለአብሮ መስራት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በግልፅ ተወያይቶ፣መግባባት ተፈጥሮ እና ውል ተበጅቶለት ካልተጀመረ የምርጫ ክልሎችን መከፋፈሉና ዕጩዎችን በጋራ ማቅረቡ አጨቃጫቂ ይሆንና ፓርቲዎቹ በጋራም ሆነ በግል ጠንክረው የማይወጡበት ሁኔታ ውስጥ ይወድቃሉ::ይህን እንደምንም ተቻችለው ቢያልፉ በአገኙት የጋራና የግል የምርጫ ውጤት ላይ አንድ አቋም መያዝ ይቸግራቸውና የህዝብን ድምፅ ማስከበር ያቅታቸዋል::

በተአምር ይህን ማለፍ ቢችሉና ያገኙት የጋራ ውጤት መንግሥት ለመመስስረት የሚያበቃቸው ቢሆን እያንዳንዱ ፓርቲ ፓርላማ የገቡ አባላቱን እያሰበ በሚፈጠረው አለመግባባት መንግስት ለመመስረት እስከ አለመቻል ተደርሶ ሐገሪቷ መልሳ በተሸናፊው ሀይል እጅ እንድትወድቅ የምትዳረግበት አጋጣሚ ሊፈጠር እንደሚችል ለመስጋት የትናንት ተመክሮአችን በቂ ነው:: ስለሆነም ተቀናጅተናል በማለት እናገኘዋለን ብለው ከሚያስቡት የፕሮፓጋንዳ ጥቅም ባሻገር ለዘላቂ ጥቅም እያሰቡ መስራት ይጠበቅባቸዋል::

በሀሳብ መለየትን ሥልጣን መጋፋት አድርገው በማሰብ ከፍረጃ ፖለቲካና ከዕገዳ ርምጃ ያልተላቀቁ ፖለቲከኞች ምኒልክ ቤተ-መንግስት በር ላይ ደርሰው ከመከከላቸው አንዱን ተስማምተው ለወንበሩ ሲያበቁ ማየት ከቻልን መታደል ነው::ለዘመናት አብሮን የኖረውም የዚህች ሐገር ርግማን ተሻረ ማለት ይሆን ነበር::ለዚህ እንድንበቃ ምኞታችን ቢሆንም በምኞት ብቻ ከውጤት አይደረስምና ተጣማሪ

ፓርቲዎች ለምን ዓላማ እንደሚጣመሩ የሚታገሉለት የጋራ ግባቸው ምን እንደሆነ ይህን ተፈፃሚ ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ የሚገዙበትን ሕግ ግልፅ ማድረግ አለባቸው:: በፕሮግራሞቻቸው ካሰፈሩዋቸው ዓላማዎቻቸውም የሚስማሙባቸውን፣ላለመስማማት ተስማምተው በይደር የሚያቆዩዋቸውን፣ፈፅሞ ሊስማሙባቸው የማይችሏቸውን የፖሊሲ ጉዳዮች ለይተው በግልፅም አንጥረው ለአባሎቻቸው ብሎም ለመራጩ ሕዝብ መግለፅ ይጠበቅባቸዋል::

የአብሮ መስራቱ ዓላማ ምርጫን በጋራ መቅረብ ከሆነ ጋርዮሽ የፈጠሩት የሁሉም ፓርቲዎች አባላት በምርጫ ዘመቻው በዕኩል አቅምና አቋም ሊሰለፉ መቻል አለባቸው:: ስለሆነም ተመሳሳይ ቋንቋ ተናግረው በአንድነት መንፈስ ተሰልፈው የምርጫውን ሂደት ሊያሳኩ የሚችሉት ፓርቲዎቹ የተስማሙባቸውን እና የተለያዩባቸውን ጉዳዮች ከነምክንያታቸው በግልጽ ማወቅ ሲችሉ ነው:: በአንድ የክርክር መድረክ ላይ «የአንተ ፓርቲ የመሬት ባለቤትነት መብት እስከ መሸጥ መለወጥ መድረስ አለበት ይላል እገሌ የሚባለው የመድረኩ አባል ፓርቲ ደግሞ መሬት የመንግስትና የሕዝብ ነው ይላል::ብታሸንፉ ተግባራዊ የምታደርጉት የቱን ነው »ተብሎ የሚጠየቅ ሰው ግልፅና የማያሻማ መልስ መስጠት ካልቻለ የመራጩን ሕዝብ ድምጽ ማግኘት አይቻልም:: እንደትናንቱ በቃላት ደልሎ ያልሆኑትን መስሎ የሕዝቡን ድምጽ ማግኘት ዛሬ በጣም አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል አስቀድሞ ማወቅና መዘጋጀት ለግል ስልጣን ሳይሆን ለሐገራዊ ድል ከሚሰሩ ፖለቲከኞች የሚጠበቅ ነው::

የአባላትንና የደጋፊዎችን ብሎም የሕዝቡን ቀልብ ለመሳብ እየተባለ የማይስማሙባቸውን ጉዳዮች ሁሉ በቃላት እያለባበሱ ማቅረብ ግን በትናንት መንገድ መሄድ ነው የሚሆነው::ነገ በተግባር መጋለጥ ሊመጣ ዛሬ መዋሸት ለምን?

መቀናጀት የሚፈጠረው በአዋጁም እንደተገለፀው ለተወሰነ ጊዜ እና በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ በመሆኑ የግድ በሁሉም ጉዳዮች ላይ መስማማት አያስፈልግም:: የሚስማሙበትንና የማይስማሙበትን ጉዳይ ግን ለይቶ ማውጣት በጣም በጣም አስፈላጊ ነው:: ለአጭር ጊዜ ፍላጎት ወይንም ግብ ተብሎ ረዥሙንና መሰረታዊውን ጉዳይ የሚያበላሽ ተግባር መፈጸም ተገቢ አይሆንም::በ «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው» አስተሳሰብ የሚካሄድ ፖለቲካ፤ ዘመን አልፎበታል:: ጥምረት የሚፈጸመው «ከፊታችን ያለውን ተራራ በጋራ ለመግፋት» በሚል አስተሳሰብ ሳይሆን መሰረታዊ የሥርዓት ለውጥ በማምጣት አስተማማኝ የዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባት በሚል ዕምነትና ዝግጁነት መሆን ይኖርበታል::

**/አቶ ታምራት ታረቀኝ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ አባልና የፓርቲው የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ ነበሩ/**

# የመድረክ አገራዊ ዓላማ በአፍራሽ ጽሁፍ አይቀለበስም

*በነብየልዑል ኢሣያስ*

ይህ ጽሁፍ አቶ አስቻለው በላይ በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ (ጥቅምት 17፣ 2002 ዓ.ም) ላይ «አንድነት» እና «መድረክ» በሚል ርዕስ ያወጡትን ትችት ይመለከታል።

አቶ አስቻለው በጽሁፋቸው የመድረክ ሰነዶች ለምርጫ ቦርድ ለምን እስካሁን አልቀረቡም? ብለው ይጠይቃሉ። ሰነዶቹ መስከረም 30፣ 2002 ዓ.ም ከተፈረሙ ለምርጫ ቦርድ አቅርቦ ሕጋዊ ዕውቅና ለማግኘት ለምን እስካሁን ዘገዩ? ነው የሚሉት። ጥሩ ጥያቄ ነው፣ ግን መዘግየቱ የመድረክን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ስህተት አይደለም፤ ያልተሟሉ ነገሮችን ለማሟላት ይሆናል የዘገየውና ይህ አስተዳደራዊ ችግር ተጋንኖ መወሳት ያለበት ጉዳይ አይመስለኝም። በዚህ አነስተኛ ጉዳይ ሰበብ ግን አቶ አስቻለው አላስፈላጊ የሆኑ የዘለፋ ቃላትንና ሐረጉችን ተጠቅመዋል። «የጓዳ ሥራ»፣ «ወደ ቤተ-መንግስት ለመግባት»፣ «የፓርላማ ደመወዝተኛ ለመሆን»፣ «የጠገበው ወርዶ የተራበው አምባገነን ለሥልጣን እንዲበቃ» ፣ «ከእኛ ይልቅ ብር የሚሰጧቸውን»፣ ወዘተ የሚባሉ አነጋገሮችና አገላለፆች ለምን አስፈለጉ? የኢትዮጵያ ምሁራን ተብዬዎች ካለስድብ ሌላ የሚያውቁት ቋንቋ የለም ማለት ነው? ሰነድ በማቅረብ ረገድ መዘግየት በመፈጠሩ እነ ዶ/ር መረራ፣ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ፣ ኢ/ር ግዛቸው፣ አቶ ቡልቻ ደመቅሳና፣ አቶ ገብሩ አሥራት፣ ወዘተ ይህን ያህል የስድብ ውርጅብኝ የሚወርድባቸው ለምንድን ነው? እነዚህ ሰዎች በመድረክ ዙሪያ የተሰባሰቡት እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ለሚጠይቅ የፖለቲካ ትግል ነው፤ ዶ/ር መረራ አሜሪካ ሄደው አንዱ ዩኒቨርሲቲ ተቀጥረው በወር አርባና አምሳ ሺ. ብር ማግኘት አቅቶአቸው ነው እዚህ ለሶስትና አራት ሺ. ብር ሕይወታቸውን መስዋዕት ለማድረግ የተዘጋጁት? ለመሆኑ አቶ ቡልቻ ናቸው ለአራት ሺ. ብር ደመወዝ እዚህ አደገኛ የፖለቲካ ትግል ውስጥ የገቡት? ምንአል ለምንናገረው ነገር ለከት ቢኖረው?

አቶ አስቻለው ቀጥለውም እንዲህ ይላሉ፤

> «ሰልፍ የተወጣባቸው የመድረክ አመራሮችም ሆኑ የግቢው ባለቤትና ለሰልፉ ምክንያት የሆኑት የአንድነት አመራሮች በር ዘግተው ስብሰባቸውን ቀጠሉ እንጂ ጥያቄያችሁ ምንድን ነው? ብሎ ብቅ ብሎ ያነጋገራቸው አንድም ሰው ያለመኖሩን ተሰላፊዎቹ በምሬት ሲናገሩ ሰምተናል አንብበናል።»

ከአንድነት ራሱን በአንጃነት ሳገለለው ቡድን የአንድነት አመራር አጭርና ግልጽ መልስ ሰጥቶአል፤ «በአንድነት ምክር ቤት በድምጽ ብልጫ ተሸንፋችሁ አንድነት የመድረክ አባል ሆኗል፣ ለአብላጫ ድምጽ የማትገዙ ከሆነ ምንም ማድረግ አይቻልም።» ብሎ እቅጩን ነግሯቸዋል። ከአንድነት ሳይወጡ ክርክራቸውን መቀጠል ይችሉ ነበር፤ ግን ይህንን ከማድረግ ይልቅ በአንጃነት መፈረጅን ነው የመረጡት። እንዲያውም፣ አንድ ሰሞን አገራዊ ጉዳዮችን ወደ ጐን ትተው «አንዲት የጽዳት ሰራተኛ ያላግባብ ከሥራ ተባራለች» እንደዚሁም አንዲት ፀሐፊ በተመሳሳይ ታግዳለች በማለት አንድነት ለያዘው አገራዊ አጀንዳ የማይመጥን አስተዳደራዊ ትርኪምርኪ እያነሱ ሁከት ለመፍጠር ሞክረዋል። እነዚህ ሰዎች ናቸው ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉት፤ ሠልፉን የማድረግ መብታቸው ተከብሯል፤ ለጥያቄያቸው መልስ ግን ተደጋግሞ

የተሰጣቸው ስለሆነ፣ ሌላ መልስ መስጠቱ ፋይዳ አልነበረውምና ሰልፉ በአግባቡ ተመዝግቦ በዝምታ ታልፏል::

አቶ አስቻለው ለጥቀው እንዲህ ይላሉ፤

«አሁን ደግሞ ከሰነዱ ምርጫ ቦርድ መግባት ይልቅ አዲሱ ሊቀመንበር ወደ አሜሪካ ለመሄድ መዘጋጀት ቀዳሚው ዜና መሆኑ እየተደመጠ ነው:: የቅድሚያ ትኩረት ለዲያስፖራው::»

አቶ አስቻለው፣ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ (በውጭ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያዊያን) በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው በደንብ የሚታወቅ ነው:: ሊቀመንበሩ ውጭ አገር (አሜሪካ) ሄደው ስለመድረክ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፕሮግራም መግለጫ ሰጥተው ድጋፍ ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት በጣም የሚደገፍ ነው፤ ድጋፉ የሞራልም ቁሳዊም እንደሆነ ይታወቃል፤ መድረክ እኮ የሚወዳደረው ለፖለቲካ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ በመንግስት ገንዘብና መዋቅር በስፋት ከሚጠቀመው ከኢህአዴግ ጋር መሆኑን አትርሱ::

«ፊርማ አሰባስበው ጥያቄ ያቀረቡ የፓርቲው አባላትን 'ወያኔዎች ናቸው' ማለታቸው በአገር ውስጥም በውጪም ተደምጧል»:: ይህን የሚሉት አቶ አስቻለው ናቸው:: የአንድነት አንጃዎች፣ ከአንድነት ጋር መዝለቅ አንችልም ካሉ፣ አንድም የራሳቸውን አዲስ ፓርቲ መፍጠር ይችላሉ፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ ሕብረ-ብሔር ብቻ የሆኑ ፓርቲዎችን መቀላቀል ይችላሉ:: ከዚህ ውጪ ሁከት መፍጠር የሚጠቅመው ኢሕአዴግን ስለሆነ ለአንጃው ሌላ ስም ለመስጠት ያስቸግራል::

አቶ አስቻለው በመድረክ መለስተኛ ፕሮግራም ላይ በ1997 ዓ.ም ቅንጅት ስለከፈለው መስዋዕትነት በብቃት አልተገለፀም የሚለውን ትችት በመደገፍ አንድነትን ኮንነዋል፤ መለስተኛ ፕሮግራሙ በመድረክ ጠቅላላ ጉባኤ ስለፀደቀ እንደገና ሊስተካከል አይችልም ይላሉ:: ጉዳዩን አስመልክቶ የአንድነት አመራር ግድፈቱ ወደፊት ሊስተካከል ይችላል የሚል መልስ ሰጥቷል:: አቶ አስቻለው ግን «ይህን ትልቅ ጉዳይ በመድረኩ ሰነድ ሳይጠቀስ ያለፈው» እያለ ግድፈቱን የሞት-የሽረት ጉዳይ እንደሆነ አጋንነው ይተቻሉ:: ጉዳዩ የሞት-ሽረት አይደለም፣ የሞት-ሽረቱ ጉዳይ በ2002 ዓ.ም በነፃ ምርጫ ሥልጣን ከኢህአዴግ መንጠቅ ነው! ይህን ለማድረግ ደግሞ ከመድረክ የተሻለ የፖለቲካ ድርጅት አይታይም!

አቶ አስቻለው ቀጥለው ዋና ጉዳይ ያነሳሉ፤ እንዲህ በማለት፤

«በመሠረታዊ በሆኑት የግለሰብ ነፃነት፣ በፌደራሊዝም፣ በመሬት ባለቤትነት፣ በመንግስት አደረጃጀት ልዩነት እንዳለው የሚገልፀው የአንድነት ሥራ አስፈፃሚ ማብራሪያ ሰነድ ይህንን ልዩነታችንን በቃለ ጉባኤ አስመዝግበናል ይላል:: የመድረክ ማኒፌስቶ የሚገልፀው ደግሞ የመድረክ አባላት በጋራ ለተስማሙበትና በማኒፌስቶው ላሰፈሩት ተፈፃሚነት ሁሉም ተገዥ እንደሚሆኑና ምርጫውን ቢያሸንፉ የጋራ መንግስት እንደሚያቋቁሙ ነው:: በልዩነት አስመዝግበናቸዋል የሚሉዋቸው ልዩነቶች በምርጫ ካሸነፉ በኋላ የት፣ እንዴትና በምን ሁኔታ ነው የሚታረቁት?»

አቶ አስቻለው መድረክ፤

- መገንጠልን አይደግፍም፤ ስለሆነም አንቀጽ 39ን ይሽራል፣
- አሰብ የኢትዮጵያ ወደብ ነው ብሎ ያምናል፤ በመሆኑም በሰላማዊና ሕጋዊ ድርድር ወደቡ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ይጥራል፣
- መሬት በግል ሊያዝ ይችላል ብሎ ያምናል፤ ይህም አንድ ወደፊት የሚያስኬድ የአስተሳሰብ እመርታ ነው («መሬት የግል የሚሆነው በመቃብሬ ላይ ነው» ብሎ ችክ አይልም)፣
- ኦሮምኛ/አፋን ኦሮሞ/ የመላ-ኢትዮጵያ መግባቢያ ቋንቋ ሊሆን ይገባል ብሎ ያምናል (ማለትም እንደ አማርኛ)፡፡ እነዚህ በጣም ክብደት ሊሰጣቸው የሚገባ ጉዳዮች ናቸው፤ ከኢሕአዴግ አስተሳሰብ በጣም የተለዩ ናቸው፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ነጥቦች ብቻ እንኳን መድረክ ሊደገፍ የሚገባ ድርጅት ነው፤ ከዚያም በላይ የቀድሞ የሕወሓት አባላት የመድረክ አባል ሆነዋል፣ ሕወሐትን በትግራይ በሚገባ መወዳደር የሚችል ፓርቲ (አረና) ተፈጥሮ የመድረክ አባል ሆኗል፡፡ በነፃ ምርጫ አረና በጣም ወሳኝ ሚና የሚጫወት ነው፣ ነፃ ምርጫ የሚካሄድ ከሆነ አረና በትግራይ እንደሚያሸንፍ አልጠራጠርም፡፡ እንዲያውም ነፃ ምርጫ እንዲካሄድ ወሳኝ ሚና ሊጫወት የሚችለው አረና ነው፡፡ አረና ከወዲሁ በትግራይ ተገቢውን ቅስቀሳ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

መድረክ ሥልጣን ከያዘ በኋላ እርሶ አሁን አክብደው የሚያዩዋቸው ጉዳዮች ሁሉ እስከዚህ ከባድ አይሆኑም፤ ለምሳሌ እነ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ኦሮምኛ የመላ-ኢትዮጵያ መግባቢያ ቋንቋ ይሁን ብለው ቢጠይቁ፣ አንድነት እንደዛ የሚሆን ከሆነ የጐሳ ክልሎች ይቅሩ ብሎ ሊደራደር ይችላል፤ ይህ ክርክር ያስኬዳል፣ ምክንያቱም ኦሮምኛ እንደ አማርኛ በትምህርት ቤቶች እንደ አንድ ትምህርት የሚሰጥ ከሆነና ከጥቂት ዓመታት በኋላ በመላ ኢትዮጵያ እንደ አማርኛ የሚነገር ከሆነ፣ «ኦሮሚያ» የሚለው ብቻውን ምንም ትርጉም አይኖረውም፡፡ ለማንኛ ውም መድረክ ሥልጣን ሲይዝ በደንብ እንከራከርበታለን፡፡ እናንተም የሆነ ያልሆነ ምክንያት እየፈጠራችሁ መድረክን ለማዳከም አትሞክሩ፡፡ የአረና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ገብሩ አሥራት በተናገሩት ጥቅስ ልደምድም፡፡ እሳቸው እንዲህ ነው ያሉት፡-

«በብሔር ማሰብ የጐዳው መሆኑን በተለይ ወጣቱ ተረድቷል፡፡ ይህንን ያሉት ኢ/ር ግዛቸው አይደሉም፣ የአረናው አቶ ገብሩ ናቸው፡፡ ኃያሉ እግዚአብሔር ይህንን ቀና አስተሳሰብ በሁላችንም ዘንድ ያሳድር!

# የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች በዴሞክራሲ ያምናሉን?

በባሪ ማሉን

ጊዜው እ.ኤ.አ መጋቢት 20/ 1878 ዓ.ም ነበር፡፡ ሁለቱም የኢትዮጵያ ታላላቅ ነገስታት አጼ ዮሐንስና አጼ ምንልክ በመካከላቸው ለዘመናት የነበረውን ልዩነትና አለመግባባት ለመፍታት ፊለፊት ተገናኙ፡፡ እነዚሁ ታላላቅ ነገስታት ለመጀመሪያ ጊዜ ፊትለፊት ሲገናኙ አንድ አዝማሪ

«የመከራው ዘመን ገና ነው፤

የተቋጨ ቢመስልም መልሶ ያው ነው» ሲል ተቀኘ፡፡

አዝማሪው እንዳለው የኢትዮጵያ የዘመናት ጉዞ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ከመከራ የጸዳ ሊሆን ከቶ አልቻለም፡፡

ኢትዮጵያዊያን በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ጎልተው የሚነሱ አዎንታዊም አሉታዊ ታሪኮች አሏቸው ከነዚህም ውስጥ እ.ኤ.አ በ1896 በኢጣሊያ የቅኝ ገዢዎች ላይ ድል ያደረጉበት የአድዋ ጦርነትና አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያዊያን ለህልፈት የዳረገው በአገሪቱ ታሪክ በአሰቃቂነቱ ወደር የሌለው የ1977ቱ ረሐብ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ሰሞኑን ይህቺ ታላቅ አገር በጽሁፌ መግቢያ ላይ የጠቀስኩት አይነት ታሪክ (ከመቶ አመት በኋላ) አስተናግዳለች፡፡

ባለፈው ሳምንት በጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሚመራው ገዢው ፓርቲ (ኢህአዴግ) በመጪው ግንቦት ለሚካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ የሚሆን የምርጫ ስነምግባር ደንብ ከሦስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ተፈራርሟል፡፡ ከሦስቱም ፓርቲዎች መካከል ሁለቱም «የገዢው ፓርቲ አዳማቂዎች ናቸው» እያሉ አንዳንዶች ትችት ይሰነዝሩባቿል፡፡ «መድረክ» በሚል መጠሪያ የሚታወቀው የስምንት ፓርቲዎች ጥምረት የዚሁ ድርድር አካል እንዲሆን በዲፕሎማቶች አግባቢነት ጥሪ ቢቀርብለትም ጥረቱ ሊሳካ አልቻለም፡፡

መድረኩ የድርድሩ አካል መሆን ያልቻለው ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ስለማሻሻል እንዲሁም ተቃዋሚዎች በመንግስት መገናኛ ብዙሐን ተገቢውን የአየር ሰዓት ድልድል እንዲያገኙ የሚያስችል ነጥብ በሰነዱ ውስጥ አልተካተተም በሚል ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ወገኖች እንደሚገምቱት የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ከገዢው ፓርቲ ተወካዮች ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ መደራደር ፈጽሞ አይዋጥላቸውም፡፡ በራሳቸው በተቃዋሚዎች መካከል ያለው ስር የሰደደ ሽኩቻና መጠላለፍም ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ስለዴሞክራሲ አውርተው አይጠግቡም፡፡ ሆኖም የዴሞክራሲ መገለጫ የሆነው ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በዚያች አገር ታሪክ ተካሂዶ አያውቅም፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ስለዴሞክራሲ ያውጃል፡፡ ነገር ግን የተቃዋሚ አባላትና ደጋፊዎችን በማዋከብ ስሙ ተደጋግሞ ይነሳል፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም እንዲሁ ስለ ዴሞክራሲ ሌተቀን ይሰብካሉ፡፡ ሆኖም እንዴት እንደሚተገበር በስልጣን ላይ ካሉት ጋር ለመነጋገር አንዳች ፍቃደኝነት

አይታይባቸውም:: በዚህ መልኩ የሚገኘን ውጤት በጋራ ለማጣጣም በሁለቱም ወገን ዝግጁነትም ሆነ ፍቃደኝነት የለም::

ባለፈው ሳምንት የአገሪቱ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር የሆኑት አቶ በረከት ስምዖን «ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ እያንሰራራ እንደሆነ እሙን ነው» ነበር ያሉኝ:: አክለውም «ይህ መንግስት እንከን የሌለውና ፍጹም ነው ልልህ አልችልም ግን ያ እንዳለ ሆኖ ወደፊት እየገሰገስን ነው» ሲሉ አስተያየት ሰጥተውኛል::

በተቃዋሚዎች በኩል የሚደመጠው አስተያየት ደግሞ ከዚህ ፍጹም የተለየ ነው:: ተቃዋሚዎቹ እንደሚሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ደብዛው ጠፍቷል በማለት መንግስትን ተጠያቂ ያደርጋሉ:: የምርጫ ስነምግባር ደንብ ድርድሩም ቢሆን የምዕራባዊያንን ቀልብ ለመሳብ እና መጠነ ሰፊ እርዳታ ለማግኘት ሲባል የተደረገ ማስመሰያ ነው ይላሉ እነኚሁ ተቃዋሚዎች::

በ1997 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ በገዢው ፓርቲ እና ዋነኛ ተቃዋሚ በነበረው ቅንጅት መካከል በተፈጠረው የምርጫ ውጤት ውዝግብ መጠነ ሰፊ ቀውስ መፈጠሩና ወደ 200 የሚጠጉ ሰላማዊ ሰልፈኞች በመዲናዋ አዲስ አበባ መገደላቸው ይታወሳል::

ያነጋገርኳቸው በርካታ ኢትዮጵያዊያን በ1997ቱ ምርጫ ድምጽ ሰጥተው ማግኘት የሚገባቸውን ውጤት ባለማግኘታቸው ተስፋቸው እንደመነመነ ገልጸውልኛል:: እነዚህ አስተያየት ሰጪዎች አክለውም ከ1997ቱ ምርጫ ወዲህ በአገሪቱ ሁለት አይነት (በኢህአዴግና በተቃዋሚዎች መካከል) የከረረ ጽንፍ መፈጠሩን አጫውተውኛል::

በአዲስ አበባ የሚገኙ ዲፕሎማቶች መድረክ ከገዢው ፓርቲ ጋር እንዲደራደር ግፊት በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: አቶ መለስ ለድርድር ዝግጁ የሆኑት በቀና ልቦና ተነሳስተው እንደሆነም ዲፕሎማቶቹ ለመድረክ አመራሮች እየገለጹላቸው ነው:: ባለኝ መረጃ መሰረት የኢትዮጵያ መንግስት መድረክ ወደ ድርድሩ እንዲመጣ በሩን ከፍቶ በመጠባበቅ ላይ ነው:: ስለዚህ በመካከላቸው ያለው የአክራሪነት ጽንፍ የፈለገውን ያህል መራር ቢሆንም የዛሬዋ ኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ከአንድ ክፍለዘመን በፊት ከነበሩ አያቶቻቸው (ከእነ አጼ ዮሐንስና ከእነ አጼ ምንልክ) ትምህርት በመውሰድ ቁጭ ብለው ስለ አገራቸው የማይነጋገሩት ለምንድነው? ሁሉም ወገን በየፊናው ስለ ዴሞክራሲ አስፈላጊነት እየደሰኮረ የዚያች ድሀ አገር የነገ ተስፋ እንዲለመልም ግን ተባባሪ መሆን ካልቻለ ተወያይቶ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለመጠቆም ፍቃደኝነቱን ካላሳየ በምን አግባብ ነው ለዲሞክራሲ መቆሙን የሚያሳየው?

/ባሪ ማሉን፣ በኢትዮጵያ የሬውተርስ ዘጋቢ ነው/

# ቁም ነገሩ ያለው ቁምነገሩ ላይ ነው

*በፍስሐ ያዜ*

ይህ ለገዢው ፓርቲ ምክር አይደለም፣ ማስጠንቀቂያም አይደለም፣ ማሳሰቢያ ልንለውም አንችልም:: ከዚህ ይልቅ ማስገንዘቢያ ወይም የግንዛቤ ማስጨበጫ ብንለው ይሻል ይመስለኛል::

ብዙ ጊዜ ገዢው ፓርቲ ከስህተቱ ለመማር ሲውተረተር ይስተዋላል:: ነገር ግን ከስህተት መማር ማለት የግድ ሲሳሳቱ መኖር ማለት አለመሆኑን የተረዳው አይመስልም:: ኢህአዴግ ከ4 ሚሊዮን በላይ አባላት እንዳሉት በኩራት መግለጽ ከጀመረ ሰንበትበት ብሏል:: ላሉትም፣ ለሌሉትም ተቃዋሚዎች የ«ተስፋ ቁረጡ» አይነት ማስፈራሪያ ይመስላል::

እርግጥ ነው ኢህአዴግ 4.5 ሚሊዮን ደጋፊዎች አይደለም ከፈለገ 70 ሚሊዮን ደጋፊና አባላት እንዲኖሩት ማድረግ ይቻላል:: ቁም ነገሩ ግን ይህ አይደለም:: ቁም ነገሩ ያለው የአባላቱ ምልመላ የትኛውን ዘዴ የተከተለ ነው? የሚለው ላይ ነው::

እንኳን በፖለቲካው መስክ በሐይማኖት እንኳ ቢሆን ብዙዎቹን በተለያዩ ነገሮች አሳምኖ እያጠመቁ ተከታይ ምዕመናንን ማብዛት ይቻላል:: ቁም ነገሩ ግን በእርግጥ ይህ ሁሉ ምዕመን ሐይማኖቱ ገብቶታል ወይ? አምኖበታል ወይ? የሚለው ነው::

በደንብ እንደሚታወቀው ገዥው ፓርቲ እነዚህን ሁሉ አባላት በምን መልኩ እንደመለመላቸውና እንዴት እንዳጠመቃቸው ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጀምሮ እስከተለያዩ መ/ቤቶች የሔደበትን መንገድ በቀላሉ ማወቅ ይቻላል - ተችሏልም::

ደማካ ጎንን ተገን በማድረግ የተመለመለ አባል ደግሞ በእጅ እንዳለ ሐብት የሚቆጠር አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

የአባላት ቁጥር ለማብዛት ደግም በአጉልና በጊዜያዊ ጥቅማጥቅሞች ከመጠቀም ይልቅ በትክክለኛውና ተጨባጭ ሀቆች ወይ የስራ ውጤቶች አማሎ መሳብ ተመራጭ መሆኑን ማወቅ አዋቂነት ነው:: ምክንያቱም በጥቅማጥቅም ደልለው ያስጠጉት ወዳጅ አስጠጊውን የሚታዘብና የሚያፌዝበት ከመሆኑም በላይ በማንኛውም ጊዜ፣ በማንኛውም ቦታ፣ ባልተጠበቀ ጊዜ በቀላሉ ሊጎዳው ሊያጠፋው ይችል ይመስለኛል::

ባጠቃላይ ፍቅርን በገንዘብ መግዛት እንደማይቻል ሁሉ፤ ቢገዙትም እንደራስ ዘላቂ ንብረት መቁጠር ያለመቻሉን ያህል የኢህአዴግ የአባላት ምልመላም አመላመሉ ሁሉ ከላይ የተጠቀሰውን ምሳሌ መሠረት ያደረገና ተመሳሳይ የሆነ ነው::

«አባል ያልሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ወደፊት ስራ የማግኘት እድላቸው የጠበበ ይሆናል» በሚል ፕሮፓጋንዳ መነሻነት በተማሪዎች መመረቂያ ጉዞ ምን ያህል የምዝገባ ወረፋ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::

ይህንና ይህን የመሰሉን አካሔድ ነው እንግዲህ እንደ ቁምነገር ተቆጥሮ ሲዘመትበት ያየነው::

ገዢው ፓርቲ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ባለፈው በምርጫ 97 ወቅት የመንግስት ዳኛ የሆነው ህዝብ ቢጫ ካርድ አሳይቶታል፡፡ አሁን በዚህ ዓመት በሚካሄደው ምርጫ ደግሞ ቀይ ካርድ እንዳያይ ሰግቷል እየተባለ ነው፡፡

እናም ያንን ስህተት መነሻ በማድረግ ከስህተቱ ለመማር ገዢው ፓርቲ የመረጠው መንገድ ደግሞ ቀይ ካርዱን መስረቅ ወይም ከዳኛው ኪስ ቀዳ ካርዱን መስረቅ ካልተቻለና ከተመልካቹ አይን መሰወር ካልተቻለ ከመስረቅ ይልቅ አጃጅሎ ወይ አታሎ፣ አልያም አባብሎ ቀይ ካርዱን መቀበል አማራጭ ሌለው አማራጭ መሆኑን የተረዳ ይመስለኛል፡፡ አካሔዱ ሁሉ ከዚህ ከላይ ካልኩት ነገር ጋር የተመሳሰለ ነው፡፡ ይህም «የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው» ከሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ባለፈ «የትም ፍጭው ብቻ በደንብ ይድቀቅ» እንደማለት መሆኑ ይገባናል፡፡

ስለዚህ ገዢው ፓርቲ አንድ መገንዘብ ያለበት ነገር አለ፡፡ ይኸውም የትኛውም አይነት መንገድ ቢጓዝ በሐቅ ላይ ባልተመሰረተ እውነት መሰል ሃሰትም ይሁን ልዩ ልዩ የማሳመኛ ዘዴ ተጠቅሞ የአባላቱን ቁጥር አብዝቶ በእነርሱ መመካት የትም ሊያደርሰው እንደማይችል ሳይጠቆም ማወቅ ነበረበት፡፡

ከዚህ ይልቅ ግን ስለተከታይና ስለደጋፊ እንዲሁም ስለአባላት ቁጥር መብዛት ከማሰብና ከመጨነቅ ለዚህም ተብሎ ጊዜንም ገንዘብንም ከማባከን ይልቅ ህዝቡ የሚፈልገውንና ከመንግስት የሚጠብቀውን ተግባር ማከናወን ይቀለው ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ ያለአንዳች ማባበያና መደለያ፣ ያለምንም የስብሰባ አባል አባል ከመሆን አልፎ ለማገዝና ለመተባበር ይጎርፋል፡፡ ትክክለኛው መንገድ ይሄ መሆኑንም የሚክድ ሰብዓዊ ፍጡር የለም፡፡

ቅዱስ መጽሃፉ እንኳን ሲመክር «ጽድቁን ብቻ ፈልጉ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል» ነው የሚለው፡፡

አዎ! ይሄ ነጭ እውነት ነው፡፡ እኔም እያልኩ ያለሁት ወይ ለማለት የሞከርኩት «መልካም ስራን ብቻ ስሩ የአባላት ቁጥሩ ይጨመርላችኋል» ነው፡፡

ለዚህም ነው ቁም ነገሩ ያለው ቁም ነገሩ ላይ ነው በሚል መነሻ እንደዜጋ የተሰማኝን በብዕር ያደማሁት፡፡

# «እንባ ጠባቂ» ተቋም፤ እንባ እያበሰ ወይስ ያልተጠየቀውን እየመለሰ?

**በኤልያስ ገብሩ**

ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በፌዴራል የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ ክስ ተመስርቶባቸው ከነበሩትና በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ መ/ቤት በእነ አቶ ተካ ገ/የሱስ የክስ መዝገብ የድርጅቱ ሰራተኞች የሆኑት 1ኛ ተከሳሽ የሽያጭና የጨረታ ኮሚቴ አባል 2ኛ ተከሳሽ የሽያጭና የጨረታ ኮሚቴ አባልና ፀሐፊ፣ 3ኛ ተከሳሽ የሽያጭና የጨረታ ኮሚቴ አባል፣ 4ኛ ተከሳሽ የላጋር ጉምሩክ ጣቢያ ተጠባባቂ የመጋዘን ኃላፊ እና ለጨረታ ሽያጭ የሚቀርቡ ዕቃዎች ዝርዝር መዝገብ አቅራቢ፣ 5ኛ ተከሳሽ በላጋር ጉምሩክ ጣቢያ ለጨረታ ሽያጭ የሚቀርቡ ዕቃዎች አጫራች፣ 6ኛ ተከሳሽ በላጋር ጉምሩክ ጣቢያ የውርስ መጋዘኖችና የሐራጅ ሽያጭ ዋና ክፍል ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ የተሰጣቸውን የስልጣን ችሎታ ከመጠን በላይ አሳልፈው በመገልገል ህገወጥ ጥቅም ለሌላ ሰው ለማስገኘትና በመንግስት እና ህዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ ጣቢያ በ16/03/91 ዓ.ም በኮንትሮባንድ ተይዘው በሞዴል 265 የደረሰኝ ቁጥር 195910 ገቢ ተደርገው ከነበሩት ለግድግዳና ለጠረጴዛ አገልግሎት የሚውሉ ፕላስቲኮች (P.V.C Sheets) ብዛቱ 877 ሮል ጥቅል መካከል በ27/07/96 ዓ.ም በጨረታ ቁጥር 034/96 እቃው ተይዞ ገቢ የተደረገበትን ለግድግዳና ለጠረጴዛ አገልግሎት የሚውል ፕላስቲኮች (P.V.C Sheets) የሚለውን የዕቃውን ስም በመቀየር የግድግዳ ወረቀት በማለት ብዛቱ 762 የሆነውን ሮል / ጥቅል ከ7ኛ ተከሳሽ ጋር በመመሳጠር የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል በሚል በተጠርጣሪነት ተይዘው በከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ወንጀል ችሎት ጉዳያቸውን ተከታትለው ስለተበየነላቸው እንዲሁም ከሳሽ የሆነው የፌዴራል የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ይግባኙን ስለተወው ፍ/ቤቱ በነፃ አሰናብቶ መዝገባቸው እንዲዘጋ በ10/4/2001 ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር፡፡

የፍርድ ሂደቱ እልባት ካገኘና ግለሰቦቹ ከተጠረጠሩበት ወንጀል በነጻ ከተሰናበቱ በኋላ ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የቀድሞ የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ ሰራተኞች ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወደ መደበኛ ስራ ገበታቸው እንዲመለሱ የፍርድ ቤት ውሳኔውን አባሪ በማድረግ በአክብሮት ያመለክታሉ፡፡ በወቅቱም ባለስልጣን መ/ቤቱ በጽሁፍ ምንም አይነት ነገር ሳይገልጽልን ወደስራ እንዳይመለሱ «ይነገራቸው» በሚል ብቻ መልስ እንደተሰጣቸው አመልካቾቹ ለአውራምባ ታይምስ ካቀረቧቸው  መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ጥያቄያቸው ተገቢውን ምላሽ በማግኘት ህገ መንግስታዊ መብታቸውን እንዳላረጋገጠላቸው ያመኑት እነዚህ ወገኖች ቅሬታቸውን ይዘው ወደ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ማምራታቸውን ይገልጻሉ፡፡

ለውድ አንባቢያን ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ የአቤቱታ አቅራቢዎቹ ዝርዝር ጉዳይ ለጊዜው ገታ አድርገን የእንባ ጠባቂ ተቋም አመሰራረት፣ ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር በጥቂቱ እንመልከት፡-

በግንቦት ወር 1990 ዓ.ም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዘጋጅነት አዲስ አበባ ውስጥ አንድ አለም አቀፍ ኮንፈረንስ ይካሄዳል የኮንፈረንሱ ዓላማ አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መነሻ በማድረግ ስለእንባ ጠባቂ ተቋም መመስረት አስፈላጊነት ሰፊ ምክክር ማካሄድ ነው፡፡ በዚሁ ኮንፈረንስ ላይ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 55/15 በሚያዘው መሰረት የዜጎችን እንባ የሚያብስ ተቋም መመስረት እንዳለበት ከስምምነት ላይ ይደረሳል፡፡

ከሁለት አመታት በኋላም ዜጎች በህግ የተሰጧቸውን መብቶች በአስፈጻሚው አካል ሳይሸራረፉ በማጎናጸፍ በግልጽነትና ተጠያቂነት ላይ የተመሰረተመልካም አስተዳደርን ማስፈን የሚል አላማ አንግቦ ይህ ተቋም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 211/1992 መሰረት ተቋቋመ።

የተቋሙ ስልጣንና ተግባር በተመለከተ ዜጎች በህገመንግስቱ የተጎናጸፏቸውን መብቶች በአስፈጻሚ አካል ስር ባሉ ተቋማት ሲሸራረፉ አስተዳደራዊ በደሎች ሲፈጸምባቸው የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች መነሻ አድርጎ እና በጥንቃቄ መርምሮ በህጉ መሰረት ተገቢውን መፍትሄ የመስጠት ኃላፊነት እንዳለበት በተቋሙ ድረገጽ ላይ የተዘረዘሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ወደ ቅሬታ አቅራቢዎቹ ስንመለስ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በጻፉት ደብዳቤ «ለተቋሙ ባቀረብነው አቤቱታ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በጽሁፍ እንዲሰጠን ስለመጠየቅ» በሚል ርዕስ ስር የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወደ መደበኛ ስራቸው እንዲመልሳቸው በጽሁፍ ማሳወቃቸውን፣ መ/ቤቱም ወደ ስራ የማንመለስበትን ምክንያት ሳይገልጽ እንደማይመለሱ «ይነገራቸው» በሚል ብቻ መልስ እንደተሰጣቸውና «ከእኛ በፊትም ሆነ በኋላ በርካታ ሰራተኞችን እንደኛው ተከሰው የነበሩና ወደ ስራ የተመለሱበት ሁኔታ እያለ እኛን መከልከሉ አግባብነት የሌለው ከፍተኛ የአስተዳደር በደል በመሆኑ ተቋሙ የደረሰበትን የምርመራ ውጤት እና መደምደሚያ ከመረጃዎቹ በመነሳት አጥጋቢ ሆኖ ከተገኘ ወደስራችን እንድንመለስ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወደ ስራችን የማንመለስበት ምክንያት በጽሁፍ ሊያሳውቀን ይገባል። እንዲሁም በተቋሙ ማቋቋሚያ አዋጅ 211/1992 አንቀጽ 26/2 የምርመራው ውጤት ከነአስተያየቱ ለአቤቱታ አቅራቢ በጽሁፍ መስጠት እንዳለበት በህጉ የተመለከተው ሲሆን ይህ ባለመፈፀሙ ወይም ባለመስጠቱ አቤቱታ አቅራቢዎች በአዋጅ አንቀጽ 27/1 መሰረት ለቀጣዩ አካል ቅሬታችንን ማሳወቅ አልቻልንም። ስለዚህ ተቋሙ በአዋጁ በግልጽ በተደነገገው የህግ አግባብ መሰረት ባቀረብነው አቤቱታችን ላይ የሰጠውን ማንኛውንም ውሳኔ እና የምርመራ ውጤት ከነአስተያየቱ እንዲደርሰን እንዲደረግ ብለው አመልክተው ነበር።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምም ነሐሴ 27 ቀን 2001 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጻፈው ደብዳቤ «ጉዳዩ እነ ዘመነ ጊዮርጊስ /4/ ሰዎች ያቀረቡትን አቤቱታ ይመለከታል» በሚል ርዕስ ተቋሙ በአዋጅ ቁጥር 211/92 በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት ዜጐች ተፈፀመብን የሚሉትን አስተዳደራዊ በደሎችን ተቀብሎ በመመርመር ተገቢውን የመፍትሄ ሐሳብ በመስጠት ላይ ይገኛል። በማለትና ግለሰቦቹ የተከሰሱበትን የወንጀል ጉዳይ ጠቅሶ የሚመለከተው ፍ/ቤትም ከተከሰሱበት ወንጀል በነፃ መሰናበታቸውንና በዚህ ምክንያትም ከስድስት ወር በላይ ከስራ ገበታቸን በመለየታቸው የስራ ውላቸውን ተቋርጧል። ይሰሩበት የነበረው መ/ቤትም የስራ ልምድ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠን ብንጠይቅም ሊሰጠን ፈቃደኛ አልሆነም ሲሉ ቅሬታ አቅርበዋል። በመሆኑም የቀረበውን አቤቱታ መርምረን የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ ይቻል ዘንድ ያላችሁን ህጋዊ ምላሽ ከተዛማጅ ማስረጃዎች ጋር ይህ ደብዳቤ በደረሳችሁ በ10 ቀናት ውስጥ ትልኩልን ዘንድ እናሳስባለን በማለት በክብርት ወ/ሮ ብስራት ጋሻው ጠና የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ም/ ዋና እንባ ጠባቂ በፈረሙበት ደብዳቤ ተገልጿል።

ቅሬታ አቅራቢዎቹም ለአውራምባ ታይምስ እንደገለፁት ከሆነ «እኛ ለተቋሙ ያመለከትነው ባቀረብነው መረጃ መሠረት ወደ መደበኛ ስራችን እንድንመለስ ካልሆነም ወደስራችን የማንመለስበት ምክንያት በጽሁፍ ባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያሳውቀን ነበር:: ሆኖም የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የፃፈው ደብዳቤ እኛ አቤቱታ ካመለከትነው ውጪ «የስራ ልምድ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠንና ለጠየቅነውም ጥያቄ ምላሽ ባለማግኘታችን ቅሬታ ማቅረባችንን ነው የገለፀው:: ይህ ምላሽ እንግዲህ ባልቀረበ ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የተሰጠና ከአቤቱታው ሃሳብ ፈጽሞ የተቃረነ ነው:: የመጀመሪያ ጥያቄያችን የስራ ልምድ ማግኘት ሳይሆን ወደስራ ገበታችን እንድንመለስ የሚል ነበር:: ወደ ስራችን የማንመለስ ከሆነም ምክንያቱ ተብራርቶ በጽሁፍ ሊሰጠን ይገባል የሚል የመሰረታዊ መብት ጥያቄ ነው:: ሆኖም ተቋሙ ከምን ተነስቶ ይህንን ደብዳቤ ሊጽፍ እንደቻለ በጣም ገርሞናል በማለት ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል::

ዝግጅት ክፍሉም ጉዳዩን ለማጣራት ወደ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በመሄድ አርብ ጥቅምት 27 ቀን 2002 ዓ.ም የህዝብ ግንኙነት ኃላፊውን ለማናገር ያደረግነው ጥረት ኃላፊው ባለመኖራቸው ባይሳካም የተቋሙ የመረጃና የህዝብ ግንኙነት ቡድን መሪ የሆኑት አቶ ገዛኸኝ ተስፋዬን አነጋግረንና በእጃችን የነበሩትን የጽሁፍ መረጃዎች በማሳየት በህዝብ ግንኙነት የሚያገለግሉበት ተቋም በጻፈው ደብዳቤ ላይ ስለተነሳው ቅሬታ ብንጠይቃቸውም «እኔ ስለ ጉዳዩ የማውቀው ጉዳይ የለም:: መረጃውን አስቀምጡልንና ጉዳዩን አጣርተን ምላሽ እንሰጣለን:: ጉዳዩን ይዘውት የነበሩትን የህግ ባለሙያዎችን እንጠይቃቸዋለን::» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል::

የተቋሙ ም/ዋና እንባ ጠባቂ የሆኑት ክብርት ወ/ሮ ብስራት ጋሻው ጠናም በጉዳዩ ዙርያ ከአውራምባ ታይምስ ለቀረበላቸው ጥያቄ «ነሐሴ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የፃፍነው ደብዳቤ ቅሬታ አቅራቢዎቹ እንዲህ... እንዲህ ተደርገን ከስራ ተባርረናል ብለው ለጠየቁት ማመልከቻ ተቋማችን የሚጠቀምበት የተለመደ ስታንዳርድ ደብዳቤያችን ነው:: ግለሰቦቹ ላመለከቱት አቤቱታ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጻፍነው ደብዳቤ እንጂ ለግለሰቦቹ በዚህ ሁኔታ መልስ አልሰጠናቸውም:: ለጉዳዩም ገቢዎችና ጉምሩክ መልስ ሰጥቶ ሊሆን ይችላል:: እኛም ጉዳዩን እየመረመርን ወይም ውሳኔ ሰጥተንበት ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን አሁን በቃሌ አላውቀውም» በማለት መልስ ሰጥተውናል:: እንዲሁም ጉዳዩ ስላለበት ሁኔታ ተጨማሪ መረጃ ለመስጠት ሌላ ቀጠሮ ሰጥተውን ነበር:: ይሁንና ለምክትል ዋና እንባ ጠባቂዋ በግልጽ የቀረበው ጥያቄ ፍ/ቤቱ በነጻ ያሰናበታቸው ወገኖች ህጉ ያጎናጽፈናል በማለት ወደ ስራቸው ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄ፤ በመስሪያ ቤታቸው ያለመፈጸሙን በመጠቆም ለተቋሙ ያስገቡት አቤቱታ ሃሳብና ተቋሙ «የስራ ልምድ እንዲጻፍላቸው በጠየቁት መሰረት»የሚል «ዕንባቸውን» ካፈሰሱበት አቤቱታ ጽንሰ ሃሳብ ውጭ ለመስሪያ ቤታቸው በምን አግባብ ተጻፈ የሚል ነበር::

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት የትምህርትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ኤፍሬም መኮንን ስለ ጉዳዩ ጠይቀናቸው ሲመልሱልን «የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ አካል ተገቢውን ምላሽ ለግለሰቦቹ ሰጥቷቸዋል:: ግለሰቦቹ ከተከሰሱበት የሙስና ወንጀል ክስ ከፍ/ቤት ነፃ ሆነናል ቢሉም በምንም አይነት መንገድ ወደ ስራቸው እንደማይመለሱ ተናግረው፤

በተመሳሳይ ጉዳይ ከስራ የተሰናበተ ሰራተኞች በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ስራ ገበታው የመመለስ መብት አይኖረውም በማለት አስተያየታቸውን አጠቃልለዋል፡፡

# ምርጫ ቦርድ ሥልጣኑን አልተነጠቀም፣ አልተጠቀመበትም እንጂ

**በግዛው ለገሠ**

በገዢው ግንባር (ኢሕአዴግ) እና በሦስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች (መኢአድ፣ ኢዴፓ እና ቅንጅት) መካከል የፓርቲዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ሥነ ምግባርን በተመለከተ ሁለት ወራት የፈጀ ድርድር ተካሄደ፡፡ ድርድሩም በስምምነት ተቋጨ፡፡ ተደራዳሪዎቹ መጪው አገር አቀፍ ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ ይሆን ዘንድ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በመስማማት ተፈራረሙ፡፡ ተያይዞም የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብና ይህንኑ ደንብ ማስፈፀሚያ መመሪያ በአራቱ ተደራዳሪዎች ተዘጋጀ፡፡

ስምምነቱም ሆነ ደንቡና መመሪያው በቀጥታ የሚገዙት አራቱን ወገኖች ብቻ ስለመሆኑ የሚክድ የለም፡፡ ይሁንና ግን የችግሩ መንስዔ የፈለቀው የሥነ ምግባር ደንቡና መመሪያው በድርድሩ ተካፋይ ያልነበሩ ፓርቲዎችን ገዢ የሚሆኑበት መንገድ በሚዘረጋበት ጊዜ ነበር፡፡ የሥነ ምግባር ደንቡንና ማስፈፀሚያ መመሪያውን የሀገሪቱ የምርጫ ሕግ አካል በማድረጉ ረገድ ሁለት አመለካከቶች ያንፀባረቁ ሁለት ወገኖች ተስተዋሉ፡፡ ሆኖም ሁለቱም ወገኖች ስለተለያዩ ነገሮች ይከራከራሉ - አንደኛው ስለደንብ፣ ሌላኛው ስለ አዋጅ፡፡

**የስምምነቱ ድምዳሜ**

ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኢሕአዴግ እና ሦስቱ ፓርቲዎች ያደረጉት ድርድር እና ስምምነት በተለያዩ መንገዶች «ታሪካዊ» ሊሰኝ መቻሉ ጥርጥር የለውም፡፡ ፊርማቸውን ያኖሩበት ስምምነትም ሕገ መንግስቱን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ ገዢ ሕጐች የተቀመጡ ጉዳዮችን ያካተተ ቢሆንም ሀገሪቱ ለነበራት የምርጫ መንፈስ ተጨማሪ ተሞክሮን እንደሚቸራት እርግጥ ነው፡፡ ነገር ግን በስምምነታቸው ድምዳሜ ላይ በስምምነቱ አማካኝነት የሚዘጋጀው የሥነ ምግባር ደንብ ወደ ፓርላማ ሄዶ ሕግ እንደሚሆን ተገልጿል፡፡ እዚህ ላይ ተደራዳሪዎቹ «የሥነ ምግባር ደንብ» ማለታቸውንና በፓርላማ የሚፀድቀው ደግሞ «አዋጅ» መሆኑን በማንሳት፣ እንዲሁም «ደንብ» ከሆነ ኃላፊነቱ የምርጫ ቦርድ እንደሆነ በመግለጽ በድርድሩ ያልተካፈሉ (እንደመድረክ ያሉት) ወገኖች ተቃውሞ እንዳላቸው ገለፁ፡፡ መቼ? ባለፈው ሳምንት ረቡዕ፡፡ የት? ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በጠራው የፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይት፡፡

## አለመደማመጥ የተስተዋለበት ውይይት

እንግዲህ ስብሰባውን የጠራው ምርጫ ቦርድ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል:: የስብሰባው ዋና ዓላማ የፓርቲዎች የሥነ ምግባር ደንብን የተመለከተ ነው፤ አራቱ ተደራዳሪዎች ያዘጋጁትን ደንብ::

የመድረክ ተወካዮች «የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ የማዘጋጀት ሥልጣን የተሰጠው ለምርጫ ቦርድ ነው» ሲሉ፣ አቶ በረከት ስምዖን ደግሞ «አራቱ ፓርቲዎች ያዘጋጁት የሥነ ምግባር ደንብ ረቂቅ እንጂ የፀደቀ ሕግ የለም»፣ እንዲሁም የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎች «ለመጪው ምርጫ የሚያግባባ የሥነ ምግባር ደንብ ለማስቀመጥ ነው ምርጫ ቦርድ መድረኩን ያመቻቸው» ማለታቸው እራሱ ምርጫ ቦርድንም ጨምሮ ሁለቱም ወገኖች ደንብን በተመለከተ ያላቸው አቋም አንድ ይመስላል:: ምክንያቱም ይህ የተዘጋጀው ደንብ አሁን ባለበት ሁኔታ የሀገሪቱን ፓርቲዎች የሚገዛ ባለመሆኑ የምርጫ ቦርድን የሥነ ምግባር ደንብ የማውጣት ሥልጣን አለመንጠቃቸው ግልጽ ነው:: ታዲያ ምርጫ ቦርድ ደንብ የማውጣት ሥልጣኑ ካልተነጠቀ ግጭታቸው ከምን ላይ ነው?

«በፓርላማው አሰራር መሠረት ሕግ የማመንጨት ተግባር ለፓርቲዎች፣ ለባለድርሻ አካላትና ለመሳሰሉት ተሰጥቷል::» የሚለው ሀሳብ ከተደራዳሪ ወገኖች ሲነሳ ርዕሰ ጉዳዩ የሥነ-ምግባር ደንብ ነው ወይንስ አዋጅ? የሚለውን ጥያቄ ይፈጥራል::

## ደንብ ወይስ አዋጅ

በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ መሠረት የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ የማወጣት ሥልጣን ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተሰጥቶታል:: ይህንን ሥልጣን የሰጠውም በፓርላማው የፀደቀ አዋጅ ስለመሆኑ ምርጫ ቦርድም ሆነ ደንቡን ያዘጋጁት ወገኖች አልካዱም፣ አይክዱምም:: አዋጅን በተመለከተ ደግሞ ሕግ የማመንጨትን ጉዳይ ማንም አያጣውም:: ነገር ግን የሥነ ምግባር ደንቡ እንደስያሜው ደንብ ሆኖና ደንብ የማውጣት ሥልጣን በፓርላማው ለምርጫ ቦርድ በግልጽ ተሰጥቶት ሳለ እንደገና ወደፓርላማው መላክ ስለምን አስፈለገ?

በርግጥ ይሄንን ሥልጣን ለምርጫ ቦርድ የቸረው እራሱ ፓርላማው ነውና ወደ ፓርላማው ሊሄድ አይችልም ብሎ መደምደም አይቻልም:: ፓርላማው ሥልጣኑን ለምርጫ ቦርድ የሰጠበትን አንቀጽ የመሻርና እራሱ ደንቡን የማውጣት ሥልጣኑ እንደተጠበቀለት ነው? ግን ለምን አስፈለገ? የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎችስ «ምርጫ ቦርድ ሕግ አያወጣም፣ ደንብና መመሪያ ሊያዘጋጅ ይችላል::» ሲሉ ምን ማለታቸው ነው:: ርዕሰ ጉዳያቸው ደንብና መመሪያን የሚመለከት አለመሆኑን እየገለፁልን ይሆን?

## ምርጫ ቦርድ

ምርጫ ቦርድ ሥልጣኑን አይነጠቅ እንጂ በአግባቡ ግን አልተጠቀመበትም:: ጉዳዩ የሥነ ምግባር ደንብ ስለማውጣት ነውና በቀጥታ የሚመለከተው እኔ ነው በማለት ወደ ፓርላማ ይሂድ የተባለውን ሀሳብ መቃወም ነበረበት:: አራቱ ተደራዳሪዎች ያዘጋጁትን የሥነ ምግባር

ደንብ ተቀብሎ የራሱን ጥናት ማካሄድ ነበረበት። (ይህንን ያስባለን አራቱ ፓርቲዎች በሚደራደሩበት ወቅት ምርጫ ቦርድ እንደታዛቢ እንኳን ባለመገኘቱ ነው።) ከዚያም የራሱን ጥናት አጠናቆ ሁሉንም የሀገሪቱን ፓርቲዎች በመጥራት «የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ላወጣ ነው» በማለት ሊያወያይ ይገባ ነበር።

ምርጫ ቦርድ አራቱ ተደራዳሪዎች ያዘጋጁት ደንብ ላይ እንዳስፈላጊነቱ ሀሳብ የመጨመርና የመቀነስ፣ እንደወረደ ተቀብሎ ረቂቅ ደንብ ማድረግ፣ አልያም እርሱን ጥሎ ሌላ አዲስ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ፓርቲዎችን የማወያየትና ደንብ የማውጣት ሥልጣን አለው። ምርጫ ቦርድ ሌላም አማራጭ አለው:- በአሁኑ ሰዓት ተጨማሪ የሥነ ምግባር ደንብ አያስፈልግም የማለት። አንድ የምርጫ ቦርድ ኃላፊ «የምርጫ ደንቦችን የማውጣት ሥልጣን የቦርዱ ነው። በሕግ የተሰጠንን ይህን ሥልጣን ማንም አልነጠቀንም።» ማለታቸው እንከን የለሽ ትክክለኛ አባባል ነው። እኚሁ ኃላፊ ቀጥለውም «በተሰጠን ሥልጣን መሠረት ከሌሎች አካላት ጋር በመነጋገር ተጨማሪ ዝርዝር የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ የማውጣት ሥልጣናችን አሁንም በእጃችን ነው» ማለታቸውም እጅግ ትክክል ነው። ይሁንና ግን የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ በፓርላማ እንደሚወጣ ተደርጐ የሕግ አመንጪዎች ዝርዝር ሲነገር የምርጫ ቦርድን ተቃውሞ አልተመለከትንም።

## አብላጫ መቀመጫ እና አብላጫ ድምጽ

የሥነ ምግባር ደንብ የማውጣት ሥልጣን የምርጫ ቦርድ ነው አልን እንጂ ወደ ፓርላማ ሄዶ ሊፀድቅ የማይችልበት መንገድ የለም፤ ምክንያቱም ቀድሞውኑ የሥልጣን ምንጭ ፓርላማው ነውና። ነገር ግን አባላቱ ለሕገ መንግስቱ፣ ለሕዝብ እና ለህሊናቸው የሚገዙበት ፓርላማ አለን የምንል ከሆነ ወደ ፓርላማውም ሄዶ ላይፀድቅ የሚችልበት እድልም ይኖራል። ይሁንና ግን ሁልጊዜ በገዢው ግንባር ኃላፊዎች ተደጋግሞ የሚነሳ ነገር አለ፤ አብላጫ መቀመጫ እና አብላጫ ድምጽ ተመሳሳይ ተደርገው ይወሰዳል። አቶ ሴኩቱሬ ጌታቸው «…ኢሕአዴግ ብቻውንም ይህንን የሥነ ምግባር ደንብ አርቅቆ ወደ ፓርላማ አቅርቦ አብላጫ ድምጽ ስላለው ተቃዋሚዎች ተቃውሞበትም ቢሆን ማሳለፍ ይቻላል።» ሲሉ በፓርላማ መቀመጫ የያዙ የኢሕአዴግ አባላት ምንም ዓይነት የመቃወም አዝማሚያ እንደማይኖራቸውና የተቃዋሚዎች በፓርላማው መገኘት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ፋይዳ እንደሌለው አመላክተዋል። ኢሕአዴግ አብላጫ መቀመጫ አለው ማለት ሁሌም ቢሆን አብላጫ ድምጽ አለው ማለት ይሆን? ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም የኢሕአዴግ አባላትም ቢሆኑ ለሕዝብና ለህሊናቸው በመገዛት ከኢሕአዴግ በተለየ ድምጽ የመስጠት እድል አላቸውና። ያም ነው ሕግ አውጪውንና ሕግ አስፈፃሚውን የተነጣጠሉ የመንግስት አካላት የሚያሰኛቸው።

## የምርጫ ሕግ አካል ስለማድረግ

ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የሚያወጣቸው ደንቦች ከሀገሪቱ የምርጫ ሕጐች መካከል አይመደቡምን? አራቱ ተደራዳሪዎች ያዘጋጁት የሥነ ምግባር ደንብ የሀገሪቱ የምርጫ ሕግ አካል ይሆን ዘንድ የአዘጋጆቹ ፍላጐት ነው። ግና ይህ እንዲሆን ደንቡ የግድ ፓርላማ መሄድ ይጠበቅበታል ብለን አናስብም። ቢሄድ እንኳን፣ በፓርላማው አሰራር መሠረት ሕግ ማመንጨት

ቢችሉም ፓርላማው በበኩሉ «እንዲወጣላችሁ የምትፈልጉት የሥነ ምግባር ደንብ ከሆነ ይህንን ሥልጣን ለምርጫ ቦርድ ሰጥቼዋለሁና እዚያው ጨርሱ» የሚላቸው ይመስለናል።

ይሁንና ግን በቀደመው የምርጫ አዋጅ ውስጥ የሚካተት የሥነ ምግባር ደንብ ነው ከተባለ (ለምን አስፈለገ የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ) ፓርላማው ሊቀበላቸው ይችላል። ተቀብሏቸውም አባላቱን አወያይቶ ሊያፀድቀው ወይ ሊጥለው ይችላል። ሆኖም ይህ ብሔራዊ የምርጫ ባርድን ከጨዋታ ውጪ ማድረግ አይሆንም? የፓርቲዎችን እንቅስቃሴ በቅረበት የሚከታተለው ምርጫ ቦርድ እያለ በፓርላማው ላይ ሥራ ማብዛት አይሆንም፤ ደግሞስ የምርጫ ሕግ አካል ለማድረግ በምርጫ ቦርድ ደንብ ሆኖ መፅደቁ በቂ አልነበረም?

## የውይይት መልካምነት

አራቱ ተደራዳሪዎች ያዘጋጁት የሥነ ምግባር ደንብ በምን መንገድ የምርጫ ሕግ አካል ይሁን በሚለው ላይ አለመግባባት ይፈጠር እንጂ «ሥነ ምግባር የጐደለው አካሄድ መከተል እሻለሁ» የሚል የፖለቲካ ፓርቲ አይኖርም። ሥነ ምግባርንም ሆነ ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ የሀገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰፊ ውይይት ቢያደርጉ መልካም ነው። ምክንያቱም ምርጫን አስመልክቶ የሚደረግ የትኛውም የፓርቲዎች ፉክክር «ህዝብ ሆይ፣ አንተን ለማገልገል እኔ የተሻልኩኝ ነኝ» ከሚል መነሻ ስለመሆኑ ይገመታል። አለዚያማ ሥልጣን ጨብጦ ህዝብን ለማስተዳደር ሳይሆን ህዝብን ለመግዛት ከሆነ ህዝቡም ደግሞ ደጋግሞ «ለውጥ መቼ መጣ» ማለቱን ይቀጥላል።

ሥልጣን ላይ የሚገኝ አካል ዓላማዬ ህዝብን ማስተዳደር ነው የሚል እምነት ካለው የተቃዋሚዎች በሀሳብ፣ በዓላማ እና በአቅም መጠናከር አያስጨንቀውም፤ የሁሉም የመጨረሻ ግብ አንድ ነውና። ስለዚህም የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት መልካምነቱ ጥርጥር የለውም። ይሁንና ግን የውይይቱ ግብ ህዝብን ዘንግቶ በፓርቲዎች (በድርጅቶች) ተጠቃሚነት ላይ ያነጣጠረ ከሆነና አለመደማመጥን ከሰነቀ ፍሬ አልባ ይሆናል። መደማመጥ ከመነጋገርና ከመሰማማት ባሻገር አንድ ጉልህ ነገር ይጠይቃል - ቅንነት።

በሌላ በኩል ከውይይቱ በተጓዳኝ በሀገሪቱ ከ90 በላይ ፓርቲዎች አሉ ቢባልም በስም እንኳ የማይታወቁ ፓርቲዎች አያሌ ናቸው። ህዝቡ የፓርቲዎቹን መሪዎች ብቻ ሳይሆን ፓርቲዎቹ ይዘውት የቀረቡትን የተለየ ሀሳብ ማወቅ ይሻል። ተቃዋሚ በመሆናቸው ብቻ ተመራጭ አይሆኑምና ከገዢው ግንባርም ሆነ እርስ በርሳቸው የሚለያዩባቸውን ነጥቦች ለህዝቡ የሚጠቁሙበት መንገድ ከወዲሁ ቢበጃጅ መልካም ነው። ገዢው ግንባር ይህንን ጨምሮ ተቃዋሚዎች ያለመሰናክል እንዲንቀሳቀሱ ማስቻሉ ነጥብ እንደሚያሲዝለት ተገንዝቦ የመንግስትነት ሚናውን ቢወጣ ሀገር ይጠቀማል።

# <u>ንግድና ኢኮኖሚ</u>

**የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት (ኢምገ) ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የብዙዎች መነጋገሪያ ሆኖ ነበር። በተለይ ቡናን የማገባየት ተግባሩን ከጀመረ በኋላ በተለያዩ ድረ-ገጾች ምርት ገበያውንም ሆነ የምርት ገበያው መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን ዶክተር እሌኒ ገብረመድህንን አስመልክቶ አያሌ ትችቶች እና አስተያየቶች ተሰንዝረዋል። ዶክተር እሌኒ «መሠረተ ቢስ» የሚሏቸውን ትችቶችና ኢምገ የሚገኝበትን ደረጃ በተመለከተ የፃፉት አለ። የርሳቸውን ጽሁፍ መሠረት በማድረግም አቶ ወንድወሰን መዝለቂያ «በኢትዮጵያ የቡና ንግድ እውነታዎችን ግልጽ ለማድረግ» በሚል ምላሽ አዘጋጅተዋል። እነሆ ለአንባቢ ይመች ዘንድ ሁለቱንም አስተናግደናል።**

--------------------

# ገበሬው የተሻለ ዋጋ ለማግኘትና ለመደራደር ራሱን በመረጃ አስታጥቋል

**በእሌኒ ገብረ መድህን (ዶ/ር)**

*አንድ የሲትያል የቡና ሊቅ ነኝ ባይ፣ ስለድሃው የኢትዮጵያ ቡና አብቃይ ገበሬ ራሱን በእጅጉ በኮፈስ ያወራል። መጣጥፎቹን በድረ-ገጾች ለንባብ ማብቃት በሚያስችሉት የቡናና ማኪያቶ መዓዛ ባወዷቸው ምቹ ካፌዎች ውስጥ ያሉ ነገሮች፣ በሚሊዩኖች የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች ክብር ያለው ሕይወት ለመኖር በየእለቱ ደፋ ቀና በሚሉባት አገራችን ውስጥ ካለው ተጨባጭ እውነታ ጋር ሙሉ በሙሉ የተለዩ ሊመስሉ ይችላሉ። ምንም እንኳን ለተወሰኑት አዝናኝ ቢሆንም፣ ከሲያትል የሚሰነዘሩ ቅጥፈቶች የተሻለ ለሚገባቸው የቡና አምራቾች አንዳች ድጋፍ የሌላቸው ናቸውና የሚቋጩበት ወቅት አሁን በመሆኑ ላይ እነዚህ ኢትዮጵያውያን እንደሚስማሙ ነው።*

*ከጥቂት ቀናት በፊት፣ በይርጋጨፌ በአንድ ታዋቂ ቡና ላኪ ባለቤትነት የተያዘ የቡና ማጠቢያ /መፈልፈያ/ ጣቢያ በጉብኝት ላይ ሳለን፣ እንኳን ደህና መጣችሁ ሊሉን (የኢትዮጵያ ምርት ገበያ - ኢምገ - ባልደረቦችን) ከመጡ ከሁለት መቶ ከሚበልጡ የቡና ገበሬዎች ጋር ለመነጋገር ያስቻለኝ የማይገኝና እጅግ አስደሳች አጋጣሚ አግኝቼ ነበር። የፀሀይዋን ፍፁም ውበት እያጣጣምኩኝ ሳለ አቶ ታደለ ለሰላምታ ወደ እኔ መጣ፤ ሰላምታ ተለዋወጥን። እርሱም፣ ያመረታቸውን ያልተፈለፈሉ (ቀያይ) የቡና ፍሬዎችን ለጣቢያው ባለቤት ሸጦላቸው የነበረ የቡና ገበሬ እንደነበረ አጫወተኝ። ስለነገሮች አካሄድ ጠየኩት። መልካም እንደሆኑ፣ ሆኖም የሸጠው ቡና ዋጋ ከፍ ያለ ቢሆን ይመርጥ እንደነበረ ምኞቱን አወጋኝ። እኔም ፈገግ አልኩና በዓለም ላይ ያለ ማንኛውም ገበሬ እንደእርሱ በተመሳሳይ እንደሚመኝ ተናገርኩ። ከዚያም የዛሬው የቡና ዋጋ ስንት እንደሆነ ጠየኩት። የመፈልፈያው ባለቤት አንድ ኪሎ ቡና በ3.50 ብር ለመግዛት ካቀረበው ዋጋ በመነሳት ገበሬዎቹ በኪሎ 4.35 ለመሸጥ እንደተደራደሩ መለሰልኝ። አስከትዬም እንዴት ያን ዋጋ እንዳወቀ ጠየኩት። የዚህን ጊዜ በውይይቱ ለመሳተፍ በፈልጉ ከ50 የሚበልጡ ገበሬዎች ተከበን ነበር። በምላሻቸውም፣ በከተማ የቡና ዋጋ እየጨመረ መሆኑን እንደሰሙ ነገሩኝ። መጨመሩን እንዴት እንዳወቁ ጠየኩ። በሬዲዮ መስማታቸውን*

ነገሩኝ:: በሬዲዮ የሰሟቸው ዋጋዎች ከየት እንደተገኙ አስከትዬ ጠየኳቸው:: ለአጭር ጊዜ ዝምታ ሰፈነ:: የሆነ ሰው በአዲስ አበባ ከሚገኘው አዲሱ ገበያ? ብሎ እያንገራገረ መለሰልኝ:: አዎ አልኩኝ፣ የእፎይታ አየር ወደ ውስጥ እየሳብሁ:: እንዲሁ ለማረጋገጥ ያህል፣ ዕለታዊውን የኢምገ የቡና የገበያ ዋጋ ስርጭት በስንት ሰዓት እንሚያዳምጡ ጠየኳቸው:: አቶ ታደለ ፊቱ ፈክቶ፣ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት አለኝ:: የተወሰኑ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት፣ ሌሎች ከረፋዱ ሰባት ሰዓት እናዳምጠዋለን አሉኝ:: አሁን እውነተኛ ጥሩ ስሜት ተሰማኝ:: አስከትዬም፣ ስርጭቱ ለመረዳት ቀላል መሆን አለመሆኑን ጠየኳቸው:: ይህን ስጠይቅ፣ ስርጭቱ በጣም ብዙ የዋጋ ዝርዝሮች፣ በጣም ፈጣን ንባብና በጣም በቀላሉ የማይገባ እንደሆነ የሚጠቃቅሱ ሀሳቦች ፈሰሱ:: እኔም መለስኩኝ፤ እሺ፣ እዚህ ከአጠገቤ የቆመው የእኛ የገበያ መረጃ ኃላፊ የሆነው አሃዱ፣ እናንተ እንደምትፈልጉት አድርጎ ያስረዳችሁዋል:: ሥራውም ነውና ላስተዋውቃችችሁ:: እናም ውይይቱ ቀጠለ::

ነጥቡ ምንድን ነው፣ ታደለና እንደእርሱ ያሉ ብዙዎች፣ ያልተፈለፈለ ወይም የደረቀ ቡናቸውን አቅራቢያቸው ወደሚገኙ የግብይት ስፍራዎች የሚወስዱት ቡናቸው ስለሚያወጣው ከፍተኛ ዋጋ፣ ስለሌሎች የዓለም ክፍሎች ወይም ሌላው ቀርቶ ስለብሔራዊ ገበያ እምብዛም እውቀቱ ሳይኖራቸው ነው:: የሚጠበቅብን እንደ አገር፣ እንደ ብሔራዊ የግብይት ሥርዓት፣ ታደለና እንደእርሱ ያሉ ሌሎች ገበሬዎች ቡናቸውን የት መሸጥ፣ መቼ መሸጥና ለማን መሸጥ እንዳለባቸው ለመወሰን የሚያስችላቸው ትርጉም ያለው ምርጫ እንዲያደርጉ መፍትሔ ማበጀት ነው፤ በመሆኑም፣ አቶ ታደለ ገቢውን ማሳደግ፣ ኑሮውን ማሻሻል፣ ልጆቹን ወደትምህርት ቤት መላክ፣ የጤና እንክብካቤ ማግኘታቸውን ማረጋገጥና ከገባበት ተደጋጋሚ የድህነት ወጥመድ መውጣት ይቻለዋል::

ታደለ የሚገባውን የተሻለ ሕይወት ይመራ ዘንድ ድጋፍ የሌላቸው መሠረተ ቢስ ወሬዎችን እንመልከት:: የመጀመሪያው፣ በኢምገ የሚከናውነው የቡና ንግድ የቡና ገበያን ውስብስብነት ምንም በማያውቁ ሰዎች በአጭር ጊዜ የተፀነሰ፣ ዝግጅት ያልተደረገበት ጉዳይ ነበር የሚል ግርድፍ ግንዛቤን የሚመለከት ነው:: መቼስ ምን ያደረጋል፣ ይሁን፣ ያኔ ገና በ1992 (እ.አ.አ) ዓለም አቀፍ የቡና፣ የስኳርና ሌሎች ምርት ገበያዎችን በተመለከተ የሥልጠና ፕሮግራም ለመቅረጽ በጄኔቫ የተ.መ.ድ ኃላፊነትን በመውሰድ የምርት ግብይት ኤክስፐርት እንደነበርኩኝና ሥልጠናውንም ከተለያዩ ታዳጊ አገሮች ለተውጣጡ ለቡና ላኪዎችና እንዲሁም ለብዙ ሌሎች ላኪዎች እንደሰጠሁ የሲያትሉ ሊቅ ያውቃል ብዬ አልጠብቅም:: እንዲሁም፣ ለዓለም ባንክ በ2001 (እ.ኤ.አ) ዋሽንግተን በሚገኘው ተቋም («International Food Policy Research Institute») ተመራማሪ በነበርኩበት ወቅት ዩጋንዳን፣ ታንዛንያንና ኢትዮጵያን ያካተተ ፕሮጀክት መምራቴን ወይም በ2002 (እ.አ.አ) በሆላንድ ድጎማ በተደረገለት ፕሮጀክት፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ በመቶዎች የሚቆጠሩ የቡና አምራቾችን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ መጠነ-ሰፊ የመስክ፣ የቤት ለቤት ጥናት ማካሄዴን ያውቃል ብዬ አልጠብቅም:: በ2003 (እ.ኤ.አ) «Getting Markets Right In Ethiopia: An Analysis of Coffee & Grain Marketing» በሚል ርዕስ፣ በሮም የገንዘብ ድጋፍ ከፍተኛ ጥናት ማከናወኔን፣ ለጥናቱም በአሁኑ ወቅት በ«US Securities and Exchanges Commission» ውስጥ የውጭ ጉዳዩች ዳይሬክተር የሆኑት ኢትዮጲስ ተፈራን

ጨምሮ በጣም ስመ ጥርና ከፍተኛ ከበሬታ ያለው የቡና ኤክስፐርት ጆን ሽልተር (በቅርብ በሲያትሉ ሊቅ ድረ-ገጽ የተገለፀው ፊሊፕ ሽልተር የንግድ አጋርና አጎት)፣ እንዲሁም በወቅቱ የኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ሴክሬታሪ ጄኔራልን ያካተተ /የስምንት ሰዎች/ የእውቅ አማካሪዎች ቡድን መምራቴን ያውቃልም አልልም:: ከኢትዮጵያ ቡና ላኪዎችና አቅራቢዎች ጋር በተደረገው ሰፊ ምክክር መሰረትነት ላይ የተመሰረተው በ2003 የተደረገው ጥናት በተለይ ጥቆማ አድርጎ የነበረው፣ ቡና በምርት ግብይት ሥርዓት አማካኝነት ቢካሄድ የተሻለ ፉክክርንና ስምምነትን (ምርት ለገዢ ከቀረበ በኃላ የሚደረግ የክፍያ ውል) ለኢንዱስትሪው በማምጣት የቡናው ንግድ እንዲሆን የሚያስችለው መሆኑን ነው::

በ2005 (እ.አ.አ) የኢትዮጵያ መንግስት የምርት ግብይት ሥርዓት ለመዘርጋት ውሳኔ ያስተላለፈው በ2003ቱ ጥናት ላይ በመመርኮዝ ነበር:: በ2006 የግብይቱን ሥርዓት መነሻ ለመፀነስ አንድ ግብረ ኃይል በእኔ ተመርቶ ነበር:: በግብረ ኃይሉ በቀረበው ሪፖርት፣ በአዲሱ የግብይት ሥርዓት ከሚካተቱ ምርቶች ውስጥ ቡና አንዱ እንደሆነ ተጠቁሟል:: እንዲሁም በተጨማሪ፣ ለተለየ የቡና አቅርቦት እየታየ ያለው የፍላጎት ዝንባሌም የተለየ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ጥናቱ አውስቶ ነበር:: እኛ አሁን የምንገኝበት ስፍራ ልንገኝ የቻልንበት ምክንያቱ ምንድን ነው፣ ከሥርዓቱ ተሳታፊዎች የመጀመሪያ መነሻ እስከ መዳረሻ ድረስ እንዴት ይህ የገበያ ሥርዓት ሊሰራ ይችላል የሚለውን በጥሞና ለአስርት ዓመታት ያህል ጥልቅ ጥናት በመካሄዱ ነው:: የሲያትሉ ሊቅ እነዚህን በጠቅላላ ሊያውቃቸው ይችላል ማለት አይቻልም:: ነገር ግን ለማወቅ መጠየቅ የአባት ነበር::

ሁለተኛው ወሬ፣ ቡና በምርት ገበያው የተካተተው መንግስት ቁጥጥር እንዲኖረው እና የቡና ገበያውን በብቸኝነት ለመምራት ዓላማ ነበር የሚለው ነው:: እዚህ ጋር የቡናው ሊቅ እውቀት እጅግ የመነመነ ነው ሚል እምነት አለኝ:: በግሉ የቡና ላኪዎች ላይ በመመስረት በውጭ ዓለም አቀፍ ድርጅት የተከናወነ ገለልተኛ የገበያ ጥናት፣ የቡና ግብይትን በተቋሙ አማካኝነት ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን ጠቁሟል:: ይህም ብቻ ሳይሆን፣ ኢምገን ያቋቋመው አወቃቀርና ሕጋዊ መርሆ የሞኖፖሊ ሥልጣንን ወይም የመንግስት ጣልቃ ገብነትን አይፈቅድም:: ሕጉ የኢምገ ባለቤትነት፣ አባላቱና አስተዳደሩ የተለያዩበት ተቋም እንደሆኑ ይገልፃል:: ተቋሙ በመንግስት ሊተዳደር እንደማይችል፣ እንዲሁም የተቋሙ አስተዳዳሪዎች የፖለቲካ ሹመኞች ወይም የሲቪል ሰርቪስ ቅጥረኞች መሆን እንደማይችሉ ሆኖም ሙያተኞች መሆን እንዳለባቸው በግልጽ ይደነግጋል:: በየትኛውም ዓይነት ግብይት ተቋሙ በመግዛት ወይም በመሸጥ መሳተፍ እንደማይችል አዋጁ በግልጽ ያስቀምጣል:: ኢምገ ራሱን ችሎ የሚሰራ ተቋም እንደሆነና በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚተዳደር እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል::

ሶስተኛው መሠረተ ቢስ ወሬ፣ ኢምገ በግለሰብ ላኪዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ መጠቀሚያ ሆኖ ነበር የሚለው ነው:: እውነቱ ይወራ እስኪ:: ዓለም ቀላል አይደለችም:: ምንም ነገር እንዲሁ ግልጽና ቀላል አይደለም:: ምንም እንኳን እዛ ሩቅ በምትገኘው ዓለም እንደዛ ሊመስል ቢችልም:: በተቋማችን አማካኝነት የቡና ግብይት ሥርዓት በተጸነሰበትና በተጀመረበት ተመሳሳይ ዓመት ዓለም አስከፊ የገንዘብ ቀውስ አጋጠማት፣ ዓለም አቀፍ የቡና ዋጋ በ30ና 40 በመቶ ወደቀ፣ ወደ ውጭ የላክነው (ለጃፓን ገበያ) ምርት 20 በመቶ የኬሚካል ዝቃጭ አለበት

በሚል ሴራ ወደቀ፣ በአገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተው የዝናብ አጣጣል የቡና ምርት በ15 በመቶ እንዲቀንስ አደረገ፣ በዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ መንሽራተት ምክንያት በይበልጥ በተከሰተው ምንዛሬ እጥረት በአገሪቱ ዋና ላኪዎች ላይ ከፍተኛ የቁጥጥር እርምጃዎች ተወሰዱ::

አራተኛው መሠረተ ቢስ ወሬ፣ ኢምገ በ2009 በዓለም አቀፍ ቡና ገዢዎች እስኪገደድ ድረስ ስለ የመለያ ቡና ንግድ አላሰበም ነበር የሚለው ነው:: ከእውነታ ፈቀቅ የሚል አንዳች ነገር የለም:: ተቋሙ በ2008 መጀመሪያ አካባቢ የኢትዮጵያ መለያ ቡና ግብይት ሥርዓት አስመልክቶ በተካሄዱ ውይይቶች ግንባር ቀደም ተሳታፊ ነበርና በሐምሌ 2008 በፀደቀው አዲሱ የቡና ሕግ ረቂቅ ላይ ባለድርሻ አካላት በግብይቱ ዙሪያ በተመካከሩበት ወቀት የኢትዮጵያ መለያ ቡና ንግድ ለማካሄድ የተለየ መንገድ መፈጠር አለበት በማለት የተከራከረ ሲሆን በዚህም አቋሙ መሠረት በ2008 ሕዳር ወር አዲስ ራሱን የቻለ ሕግ እንዲጸድቅ ምክንያት የሆነ ነበር:: ሕጉም ኢምገ የኢትዮጵያ መለያ ቡና ግብይትን እንደአስፈላጊነቱ በተናጠል ወይም በጋራ እንዲያከናውን ሥልጣን ሰጥቶታል:: በዚህም መሠረት፣ የኢትዮጵያ መለያ ቡና ግብይት በጀመርን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እቅዳችንን በአገር ውስጥ ላሉ የቡና ግብይት ተሳታፊዎች በዝርዝር የተብራራ የነበረ ነው:: በ2009 በአትላንታ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የመለያ ቡና ግብይት ዝግጅት ላይ የነበረን ተሳትፎ፣ ግብይቱን አስመልክቶ ትክክለኛ ሥርዓት የመንደፍ ጥረታችን አንዱ አካል ነበር::

የሲያትሉ ሊቅ «የኢትዮጵያን ቡና ግብይትን ማለባበስ» ብሎ ከገለፀው በተፃራሪ፣ በቅርብ ይፋ ያደረግነው የመለያ ቡና ግብይት ሥርዓትን የሚመለከተው የትግበራ እቅዳችን ንድፍ የመለያ ቡና ላኪ ከሆኑት አገሮች እጅግ ውጤታማና ሩቅ ደራሽ ናቸው ከሚባለት አንዱ ሆኖ የሚጠቀስ ነው:: የአሜሪካ የመለያ ቡና ተቀባዩች ማህበር በቅርብ ያወጣው መግለጫ «ይህ ሥርዓት ማህበሩ የቡና ምርት ከመድረሻው ሲራገፍ ማሟላት አለበት ብሎ ያስቀመጣቸውን መመዘኛዎች በሙሉ ተግባሪዊ ያደረገና ቡና ለገበያ እንዴት መቅረብ አለበት የሚለውን በተመለከተ ከፍተኛ ለውጥ መደረጉን የሚወክል ነው:: ይህ ሥርዓት የተለዩ የቡና ምርቶችን ከመገኛቸው በተሻለ ለመለየት ብቃት ያለው ሞዴል የሚሆን ነው::» ይላል:: ታደለ እነዚህን ቃላት ሲሰማ እንደሚኮራ ይሰማኛል::

ስለምን እንደሚኮራ እስኪ ልናገር:: የነደፍነው ሥርዓት ታደለ ቡናውን አቅራቢያው ወደሚገኝ የኢምገ መጋዘን በቀጥታ ማቅረብ የሚያስችለውና ያቀረበው የቡና ምርት ደረጃ የሚሰጠው ደረጃ ምርጥ ከሆነ - በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የቡናን ደረጃ ለመወሰንም የቻልነው ነው - የተሰጠውን የጥራት ደረጃ እንዲያውቅ ይደረጋል:: ከዚያም በደረጃው መሰረት ይሸጠዋል:: የሚገባውንም ክፍያ ያገኛል:: አሁን ታደለ ሶስት ምርጫዎች አሉት - እንዴት፣ የትና ለማን መሸጥ እንደሚችል የመወሰን ምርጫዎች:: ሕግ ስለሚፈቅድለትም ለዓለም አቀፍ ገዥ በቀጥታ መሸጥ ይችላል:: ቢሆንም ይህ በቀላሉ የሚከናወን አይደለምና የእርሱ ማህበራት እውቀታቸውንና ብቃታቸውን ለመገንባት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል:: ከዚህ ቀደምም ያደርግ እንደነበረው በኢምገ አማካኝነት ቡናውን ለላኪዎች ይሸጣል:: ሆኖም የቡናውን የጥራት ደረጃ አሁን ስለሚያውቀው ለተሻለ ዋጋም መደራደር ይቻለዋል:: ወይንም ከኢምገ ውጭ ላለ ለአገር

ውስጥ አቅራቢ መሸጥ ይችላል:: አቅራቢውም ከታደለ ከገዛ በኋላ በኢምገ አማካኝነት ለቡና ላኪ ይሸጠዋል:: በኢምገ አማካኝነትም አቅራቢው የገዛውን ቡና የሚሸጥበት ዋጋ ስንት እንደሆነ ስለሚያውቀው ከንግዱ የተሻለ ዋጋ ለማግኘትና ለመደራደር በመረጃ ራሱን አስታጥቋል::

በቀድሞው የግብይት ሥርዓት መሰረት ታደለ ቡናውን ለላኪ ይሸጥ የነበረው ቡናው ያለውን የጥራት ደረጃ ሳያውቀው ነበር:: ላኪውም ታደለ በማያውቀው ዋጋ ለውጭ ገበያ ያቀርበዋል:: ለታደለ ነገሮች ከተመቻቹለት፣ ከተላኪው የቡና ሽያጭ ከሚገኘው ተጨማሪ ትርፍ ድርሻውን ሊያገኝ ይችላል:: አሁን ግን ያን ግልጽ የሚያደርግ የኢምገ የክፍያ ሥርዓት በመኖሩ ክፍያው በተፈፀመ በቀጣዩ ቀን ታደለ የሚገባውን ክፍያ ያገኛል:: ይህም ክፍያውን ለማግኘት በተስፋ ሳምንታት ወይም ወራት መጠባበቅን የሚያስቀር ነው::

ያም ሆኖ ሥርዓታችን ለታደለ ብቻ የሚሰራ አይደለም:: ላኪዎችም በጣም ያተርፋሉ ምክንያቱም ገንዘባቸውን ያወጡበት ቡና ለገዢው በሰዓቱ፣ በትክክለኛ ጥራትና ብዛት መድረሱን በኢምገ ሥርዓት አማካኝነት ማረጋገጥ ይቻላቸዋልና ነው:: ለዚያም ነው ፍላጎታቸው በተመሳሳይ መሟላቱን ለማረጋገጥ ከእኛዎቹ የቡና ላኪዎች ማህበር ጋር በቅርበት እየሰራን ያለነው:: አሁን ደረጃውን/ጥራቱን የጠበቀ ቡና ከምንጩ (ከመገናኛው) የማግኛ ዘዴ ያለን በመሆኑ ዓለም አቀፍ ገዥዎችም አትራፊዎች ናቸው:: ይህም ከፍተኛ የጊዜ ብክነትንና ድካምን ያስቀራል:: ለዚህም ቡናዎቹን ከበቀሉበት የቡና አብቃይ መገኛ ሥፍራ ለማግኘት የሚያስችለው ሥርዓት ተጠቃሽ ነው:: ይህም ማለት በተገቢው ዋጋ ከገበሬዎች በቀጥታ ተሸምቷል የተባለ የኢትዮጵያ ደረጃውን የጠበቀ ቡና ለመግዛት ተጨማሪ የሚከፍሉ ተጠቃሚዎች አሁን ይህን በተመለከተ በሥርዓቱ እርግጠኞች ይሆናሉ:: ለሁሉም ከአድማስ ወዲህና ወዲያ ላሉ ግልጽነት መልካም ነገር ነው፤ እንዲሁም ለገበሬውና ለተጠቃሚው:: እናም፣ ግልጽነት ኢምገ በመሠረታዊነት የቆመለት ነው::

በይርጋጨፌ እምብርት በምትገኘው ኮቸሬ በምትባለው ተወዳጅ ገጠራማ እውቅ የቡና ስፍራ ፀሀይዋ እየጠለቀች ሳለ፣ ከነበረን አጭር ውይይት በኋላ ስንለያይ ታደለ በስሱ ፈገግ አለ:: ድንገት የኢምገ ሎጐ (አርማ) ያለበትን ነጭ ኮፍያዬን ሰጠሁት:: ተቀብሎኝ ወዲያው አደረገው:: በዚህ ዓመት የተሻለ ለመስራት ተስፋ እንዳለው ነገረኝ:: እኔም ተስፋውን ወደ ፍሬያማነት መለወጥ ሥራዬ እንደሆነ ነገርኩት::

*/ዶ/ር እሌኒ ገብረ መድህን የኢምገ መስራችና ሥራ አስኪያጅ ናቸው::/*

# በኢትዮጵያ የቡና ንግድ እውነታዎችን ግልጽ ስለማድረግ

*በወንድወሰን መዝለቂያ*

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት (ኢምገ) መስራች እና ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር እሌኒ ገብረመድህን በቅርቡ «will The Real Poor Farmer Rise» በሚል ርዕስ ያስነበቡን ጽሁፍ ብሔራዊ ጥቅምን በተመለከተ ለጠንካራ ህዝባዊ ውይይቶች መልካም አስተዋፅዖ አለው:: እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግስትን የሚደግፍ ታዋቂ ሰው በህዝብ ዘንድ ውስብስብ ስለሆኑ ጉዳዮች በሲቪል ውይይት ላይ ለመሳተፍ መምረጡ አበረታች ነው:: ይህ በኢትዮጵያ አዲስ ክስተት እንደመሆኑ ግለሰባዊ ማንነትን እና የኃላፊነት ማንነትን መነጣጠል አለመቻሉ ተቀባይነት አለው፤ ምንም እንኳን ህዝባዊ ውይይቶች እና አስተያየቶች የዴሞክራሲ ማዕከላዊ መሠረት በሆኑበት ህብረተሰብ ውስጥ ለኖሩትና፣ ይልቁንም የዴሞክራሲያዊ እና የሲቪል ግንኙነት ሞዴሎች እንዲሆኑ ለሚጠበቁት ግለሰቦች ወሰኑ ከፍ የሚል ቢሆንም:: የግል ስሜቶቻችን እና ግላዊ ፍላጐቶቻችንን ወደጐን በማድረግና ጠረጴዛው ላይ ባሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር በምሁራዊ ወይይቶች የመሳተፍን ትምህርት መቅሰም ለሁላችንም ቢሆን ወሳኝ ነው፤ በያዝነው ርዕስ ረገድ በኢትዮጵያ የቡና ሴክተር ላይ ሊከሰቱ የሚችሉት ችግሮች መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው::

በኢምገ፣ በአሜሪካ የቡና ተቀባዮች ማህበር (SCAA) እና በሌሎች መካከል ከኦክቶበር 21-24 በአዲስ አበባ የነበረው ክንውን ወቅታዊው ሁኔታ ሆኖ ሳለ ኢምገ እና የኢትዮጵያ የቡና ሴክተር ችግሮችን አስመልክቶ - ዶክተር እሌኒ እንዲሳተፉ ያደረጋቸው ርዕሰ ጉዳይ - የሚደረገው ውይይት ለሳምንታት ዘልቋል:: በዚህ ጊዜ መንግስት ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ ኢምገን መጠቀምን፣ የሀገሪቱ የንብረት መብት ሕጐች ብቃት፣ ገበሬዎችን ከብዝበዛ የመጠበቅ የመንግስት ኃላፊነት፣ የሀገሪቱን ምርጥ የቡና ብራንዶች ለገበያ የማቅረብ ስጋቶች፣ ኢምገ ብቁ የሀገር ውስጥ የግብርና ሽቀጥ ገበያ በመፈጠር ርሃብን ለማስወገድ ድጋፍ ማድረግ ከሆነው ከመጀመሪያው የተቀደሰ ተልዕኮው መዘናጋቱን፣ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችንም በተመለከተ አያሌ ጥያቄዎች ተነስተዋል:: ኢምገ በተለይም ከቡና ንግዱ ጋር በተያያዘ ትችቶች የተሰነዘሩበት ምክንያት የቡና አስተዋጽኦ (ድርሻ) ከፍተኛ መሆኑና ለቀስ በቀስ ሙከራ (trial and error) እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ነው:: መንግስት የቡና ሴክተሩን መቆጣጠሩ በአጠቃላይ ለግሉ ዘርፍ እድገትም ሆነ በተናጠል ላልተነካው የቡና ሀብት አውዳሚ ሊሆን እንደሚችል በቂ መረጃ ያላቸው የኢንዱስትሪ ታዛቢዎች አስጠንቅቀዋል:: ነገር ግን ኢምገ ምንም እንዳልተፈጠረ ዓይነት ሁሉም ነገር መልካም ስለመሆኑ የያዘውን አቋም የቀጠለበት ይመስላል:: ከላይ ከተገለፀው ጽሁፍ አንፃር በየትኛውም ዓለም ያለ ለኢትዮጵያ የሚቆረቆር ሁሉ ተመሳሳይ ግንዛቤ እና አመለካከት ሊኖረው እንዲችል አሁን የሚገኙት ችግሮች ግልጽ በሆነና ባልተዛባ መንገድ ሊነገሩ ይገባል:: ስለዚህም ኢምገ እና የቡና ሴክተሩ በሚገኙበት አጣብቂኝ ሁኔታ ሳቢያ ሊከሰት የሚችለውን የችግሮች መጠን አስመልክቶ የሚደረገውን ውይይት ቆም አድርጐ እውነታዎቹን ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል:: ለዚህም ሲባል ግልጽ ለመሆንና በኢትዮጵያ ምን ነገር መከሰቱን በተመለከተ በኢምገ ያደረውን ከፈተት ለመሙላት፣ በማስከተል ከዶክተር እሌኒ ጽሁፍ ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ነጥቦች ጐን ለጐን እንመለከተለን::

«በኢምገ የቡና ንግድ የቡና ገበያን ውስብስብነት ምንም በማያውቁ ሰዎች በአጭር ጊዜ የተፀነሰ፣ ዝግጅት ያልተደረገበት ጉዳይ ነበር::»

ኢትዮጵያ በቡና ሴክተር የበቁ ባለሙያዎች እጥረት እንዳለባት ለማመን ምንም ምክንያት ባለመኖሩ በውይይቶቹ ሁሉ የኢምገ ኃላፊዎች ብቁነት የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ አያውቅም፡፡ ይህን ማድረግ ሴክተሩን ለሶስት ተከታታይ የመንግስት ሥርዓቶች ያቆዩትን ሰዎች ክብር መንሳት ይሆናል፡፡ ይሁንና ግን ይህ መንግስት እና ኢምገ ሁኔታውን በተለከተ ጥበብ ወይም ብቃት ባለማሳየታቸው ምክንያት የመለያ (specialty) ቡና ንግድ መቋረጥን ተከትሎ የመጣውን የሚዲያ ማዕበል በአግባቡ አለመመከትን አያስቀርም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ኢምገ ለቡና ንግድ ዝግጁ እንዳልነበረና ኢምገን እውን ያደረጉት የፕሮጀክት እቅዶች በዚህ ቅርብ ጊዜ ውስጥ የቡና ልውውጥ ማካሄድን አለማካተታቸውን የሚያሳዮ ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ኢምገ የተመሠረተው ለቡና ንግድ ሳይሆን ለሀገር ውስጥ የእህል ግብይት ነበር፡፡ የመጀመሪያው ማስረጃ የሚገኘው በዶክተር እሌኒ እና በአፍሪካ ምርት ገበያ (ማላዊ) ዋና ሥራ አስኪያጅ እና በዝምባብዌ ግብርና ምርት ገበያ ፕሬዚዳንት በኢያን ጉጊን አማካኝነት በተዘጋጀው የፖሊሲ ማስፈሪያ ሰነድ ላይ ነው፡፡ በኖቬምበር 2005 የተዘጋጀው ሰነድ «Does Ethiopia Need a Commodity Exchange?: An Integrated Approach to Market Development» የተሰኘ ርዕስ ሲኖረው በ24 ገጾቹ ውስጥ አንድም ጊዜ ስለ ቡና የሚያነሳበት ቦታ የለም፡፡

በተጨማሪም የኢምገ የልምድ እና የሰው ኃይል ማነስ ለቡና ንግዱ ችግር አስተዋፅዖ ያደረጉ መሠረተዊ መንስኤዎች ናቸው፡፡ በዚያን ጊዜ የስምንት ወር እድሜ የነበረው ኢምገ ያልጠበቀውን ዓለም አቀፉን ቡና የማገባየት ተግባር በድንገት ከመንግስት ሲሰጠው በግብርና ሸቀጦች ንግድ እምብዛም ልምድ ሳያካብት የራሱን ተቋም አቋም እንኳ ገና አልገነባም ነበር፡፡ ዶክተር እሌኒ አሁን የካዱ ቢሆንም የኢምገ ተገቢነት ያለው መረበሽ ዶክተር እሌኒን ይዞ በቀረበው «PBS/Market Maker» ፊልም ተገልጾ ይገኛል፡፡ ለዚህ አስፈላጊ ከሆነው የፊልሙ ክፍል በጽሁፍ መልክ የተገለበጠውን እነሆ፡-

**ተራኪ (ኤሮን ብራውን)፡-** «የእሌኒ ኢምገን የመገንባት ስትራቴጂ ከመሮጥ በፊት በእርምጃ እንደመጀመር ነው፤ በጥቂት ሸቀጦች መጀመር፣ ጉርባጣውን ማለፍ፣ አለመድገም፣ ቀስ በቀስ ሥርዓቱ መስራቱ ሲታወቅ...፡፡ ለሳዑዲ አረቢያ ነዳጅ እንደሚባለው ለኢትዮጵያ ቡና ነው፡፡ [በ2008 የተከሰተው] የቡና ቀውስ አጠቃላይ ኢኮኖሚውን ስጋት ውስጥ ጥሎት ነበር፡፡ በከፍተኛ የመንግስት ደረጃ ጥያቄው ተነሳ፡- ኢምገ ለሁሉም ክፍት በሆነ ገበያው፣ በብቁ የዋጋ ተመን ቡናን አሁን ቢያነሳውስ? ከዓመታት በኋላ አይደለም፤ አሁኑኑ? ወደታች ማሽቆልቆሉ ይወገድ ይሆን? ለእሌኒ፣ ለቡድኗ፣ ለኢምገ ይህ አቻ የለሽ እድል እና አቻ የለሽ አደጋ (risk) ነው፡፡»

**ዶክተር እሌኒ፡-** «ከከፍተኛ የመንግስት ሰዎች ጋር ዘጠኝ ሰዓታት የፈጀ የሁለት ቀናት ጠንካራ ስብሰባ ነበረን፤ እናም በመጨረሻ ምክትል ጠቅላይ ሚስትሩ ወደኔ እየተመለከቱ «የመጣውን እንቀበል ካልን የመተግበር አቅሙ አለሽ ወይ?» አሉኝ፡፡ እኔም ወደርሳቸው እየተመለከትኩ «አዎን» አልኩኝ፡፡ ... በጣም ፈርቼ ነበር፡፡ በጣም፣ በጣም መግለጽ የሚያስቸግር ቅጽበት ነበር፡፡ ከስብሰባው ስወጣም ለማኔጅመንት ቡድኔ ስልክ ደውዬ «ሁሉንም

የኢትዮጵያ ቡና ልናሻሽጥ ነው:: ይህ ሁሉንም ነገር የሚለውጥ ነው::» በማለት ነገርኧቸው:: ... ከረጅም ጊዜ አኳያ ለኛ ይበልጥ የተሻለ ነው፣ ነገር ግን ያላወኩት ነገር ቢኖር «እንወጣው ይሆን?» የሚለውን ነው:: ... ቡና እኮ ግዙፍ የሆነ ሁኔታ ነው፤ እጅግ ጥቂት የሰው ኃይል፣ እጅግ ጥቂት ቁሳቁስ፣ እጅግ ጥቂት ጊዜ ይዞ መስራት::»

ይኼ ነው:: መንግስት የቡና የግብይቱን በምርት ገበያው በኩል እንዲያመራ ለመወሰን የወሰደበት ይኼ ነው:: ዋናው ነጥብ፣ ቡናን በምርት ገበያው የመሸጥ ውሳኔ ሙሉ ለሙሉ መንግስት የቡና ኤክስፖርት ፍሰትን ለመቆጣጠር እና ለማንሰራራት በመፈለጉ ምክንያት የተነሳሳ የፖለቲካ ውሳኔ ነው::

**«ቡና በምርት ገበያው የተካተተው መንግስት ቁጥጥር እንዲኖረው እና የቡና ገበያውን በብቸኝነት ለመምራት ዓላማ ነበር::»**

ኢምገን ያቋቋመው ሕግ የኢምገ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስድስት በመንግስት እና አምስት በግል የተሾሙ ዳይሬክተሮችን እንደሚይዝ በግልጽ ያስቀምጣል:: ምንም እንኳን አሁን በሚገኘ ው ቦርድ የመንግስትን ሥራ የመደገፍ ዓላማ ያላቸው ዳይሬክተሮች የበላይነት ቢኖራቸውም:: ከአስራ አንዱ ዳይሬክተሮች ሦስቱ መቀመጫዎች ብቻ (27 በመቶ) በግሉ ዘርፍ የተያዙ ናቸው:: የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና ቃሊቲ የምግብ ፋብሪካ (ማናጀሮቻቸው የዳይሬክተርነት ኃላፊነት ያላቸው) በግል የተሾሙ ናቸው ብሎ መከራከር ማጭበርበር ነው:: ቀላልና ቀጥተኛ:: እነዚህ ድርጅቶች በመንግስት የተያዙ ሲሆኑ በየራሳቸው የዳይሬክተሮች ቦርድ አማካኝነት በምርት ገበያው የቦርድ መቀመጫ ላለውና የመንግስት አካል ለሆነው ለፕራይቬታይዜሽን እና የመንግስት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ሪፖርት ያደርጋሉ::

የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርድች አሁን በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በቡና ንግድ ላይ ዋና ተጫዋች ነው፤ እንደ «ብሉምበርግ» ከሆነ በገዢው ፓርቲ ባለቤትነት የተያዘ ኢንዶውመንት የሆነው ጉና ትሬዲንግ ኃውስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እንዲሁ ተሳታፊ ነው:: ጉና ሴክተሩን ለአምስት ዓመታት እርቆ ከቆየ በኋላ ወደ ቡና ንግድ ለመቀላቀል መዘጋጀቱን በይፋ አሳውቋል:: እንደ ዓለም ባንክ ያሉ ገለልተኛ ተቋማት እነዚህ ድርጅቶች በፖሊሲ አርቃቂዎች ዘንድ ልዩ መብት ከማግኘት ተጠቃሚ ሊሆኑ ስለመቻላቸውና ይህም በገበያው ላይ ፍትሃዊ ያልሆነ መተማመኛ ሊሰጣቸው እንደሚችል ስጋታቸውን ሲያስተጋቡ ቆይተዋል:: ይህ ገበያውን በብቸኛ ነት የመያዝ ምልክት ካልሆነ፣ ታዲያ ምንድነው?

**«ኢምገ በግለሰብ ሳኪዎች ሳይ እርምጃ ለመውሰድ መጠቀሚያ ሆኖ ነበር::»**

ይህንን የችግሩን ምልከታ በተመለከተ ብዙ ፀሃፊዎች የሀገሪቱን የሕግ እና የፖለቲካ ሁኔታዎች ነባራዊ ሁኔታ በመመርኮዝ ብዙ ብለውበታል::

**«ኢምገ በ2009 በዓለም አቀፍ ቡና ገዢዎች እስኪገደድ ድረስ ስለ የመስያ (specialty) ቡና ንግድ አሳሰበም ነበር::»**

የመለያ ቡና ንግድን በተመለከተ ኢምገ የነበረው ሀሳብ ምንም ይሁን ምን በርግጠኝነት የሚታወቀው ነገር የኢምገ አሠራር የመለያ ቡና የውጭ ንግድን አሰናክሏል፣ እናም በማህበራት እና በንግድ እርሻዎች ከተሸጡት የተወሰኑ ክምችቶች በስተቀር ሁሉም ቡና እስካሁን የተሸጠው በሸቀጦች ዋጋ እና ገበያ ነው:: ኢምገ መፍትሔ እስከሚያበጅ ድረስ ከሀገር የሚወጣ «ብቸኛ ምንጭ» ያለው የመለያ (specialty) ቡና የለም፤ ምክንያቱም አሠራሩ የመገኘ ት ሁኔታውን አስቀርቶታል:: እዚህ ላይ ሁለት ጥያቄዎች ይነሳሉ:- 1) በኖቬምበር 2008 የወጣው ሕግ የመለያ ቡናን እንደአስፈላጊነቱ ለብቻው ወይም በአንድነት ለግብይት የማቅረብ ኃላፊነትን ለኢምገ ከሰጠውና ኢምገም መፍትሔ እስኪያገኝ ድረስ የመለያ ቡናን እንደ ሸቀጦች ለማገባየት ከወሰነ ለንግዱ መሰናከል ብቸኛው ተጠያቂ ኢምገ ነው ማለት አይደለም? 2) ኢምገ አዲስ አሠራር እስከሚዘረጋ ድረስ የመለያ ቡና ግብይቶች በዚያው እንዲቀጥሉ ለምን አልፈቀደም?

ትልቁ ችግር ኢምገ የመለያ (specialty) ቡና ብራንድ የሚሠጠው የሀገሪቱ የቡና ምርት 3.7 በመቶ አካባቢ ብቻ ስለመሆኑ ግንዛቤ ስለነበረው በገፍ (በከፍተኛ መጠን) የቡና ንግድ ላይ አተኩሮ መቆየቱ ነው:: በ2009 በአትላንታ የአሜሪካ የመለያ ቡና ተቀባዮች ማህበር (Specialty Coffee Association of America - SCAA) ዝግጅት በኋላ ነበር ለችግሮቹ መፍትሔ ለማፈላለግ የአሜሪካ የተቀባዮች ማህበር እና ኢምገ የጋራ ቡድን የመሠረቱት:: በኦክቶበር ወር መጨረሻ በኢትዮጵያ በተካሄደው የኢምገ የመለያ ቡና ዝግጅት ላይ ይህ የጋራ ቡድን ለአሜሪካ የተቀባዮች ማህበር ፕሮፖዛሉን አቀረበ:: አሁን የምንገኘው እዚህ ላይ ነው::

ቀጣዩ ምንድነው?

የቡና ግብይት ስትራቴጂው ከሸቀጥ ገበያው ባሻገር ሊመለከት ይገባዋል:: ዓለም አቀፉ የቡና ንግድ በጥቂት ድንበር ዘለል (multinational) ኮርፖሬሽኖች ቁጥጥር ስር ሲሆኑ ዓለም አቀፍ ዋጋዎችም ብዙውን ጊዜ የሚወሰኑት በነዚህ ኮርፖሬሽኖች ነው:: የቀን ተቀን የዋጋ መውጣትና መውረድ በዋነኛነት የሚፈጠረው በገዥዎች የመደራደር ኃይል እና የቡና አቅርቦት ቅድመ ትንበያ ነው፤ ቅድመ ትንበያውም በበኩሉ የዓለም የቡና አብቃይ ክልሎችን በሚነኩ መንስዔዎች ላይ ጥገኛ ነው:: ብራዚል፣ ኮሎምቢያ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ቬትናም፣ ሜክሲኮን ጨምሮ በትላልቆቹ የቡና አምራቾች መካከል የሚደረገው ፉክክር የአቅርቦት መጠንን ስለሚጨምር የዋጋ መቀነስን በመፍጠር ብዙውን ጊዜ እነዚያ ኮርፖሬሽኖችን ተጠቃሚ ያደርጋል:: እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት ኢኮኖሚያቸው በቡና ላይ ለተመሠረተ ሀገራት ጥቅሉ ውጤት የሚሆነው በቡና መላኪያ ዋጋዎች ላይ ተጽዕኖ በማሳደሩ ረገድ ምንም ማለት አለመቻላቸው ነው:: ስለዚህም ኢትዮጵያ የቡና ሀብቷን በአግባቡ ተጠቅማ ፉክክሩን ማሸነፍ የሚያስችላት ለውጥ አምጪ የገበያ ስትራቴጂ መንደፍ የኢምገ ኃላፊነት ነው::

አሁን በሚገኝበት ሁኔታና በአጭር የእቅድ ጊዜ ውስጥ ሀገሪቱን ለማገዝ ኢምገ ሊተገብረው የሚችለው ነገር ለመለያ (specialty) ቡና ንግድ ቀላል የሚሆን እና ለገበሬዎቹ ጥቅም የሚያስገኝ አዲስ አሠራር መፍጠር ነው:: ይህንን በተመለከተ የመንግስትን እና የኢምገን አፋጣኝ ትኩረት የሚጠይቁ የተንጠለጠሉ ጉዳዮች እና ያልተመለሱ ጥያቄዎች አሉ::

በቅርቡ ከአሜሪካ የመለያ ቡና ተቀባዮች ማህበር (SCAA) ጋር በተደረጉት ስብሰባዎች የተገኙትን ውጤቶችና ተካፋዮቹ የደረሱባቸውን ስምምነቶች በማጋራት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት (ኢምገ) ጠቃሚ ውይይቱን እንደሚመራ ተስፋ አለኝ።

## ሞቲቬሽን

# ጥልቅ ስሜት

**በባንቺወሰን ወልደየሱስ**

በድንገት የተገኘ ነገር አይደለም። በአጋጣሚ ወይም በዕድል የተገኘም አይደለም። በጥልቅ ስሜት ውስጥ ሆኖ የተፈጠረ እንጂ። የስራው ውጤት ከመገረም መብዛት ዓይን የሚያስጨፍን ነው። ስራው መልሶ መላልሶ በታየ ቁጥር አሁንም አሁንም የሚያስጨበጭብ ነው። አግራሞትን የፈጠረ ስራ ነው፣ 'አቤት የሰው ልጅ ብቃት' ያስባለ ስራ ነው፡ ስራው የተሰራው ከሚጠይቀው ግዴታ በላይ ነው፣ ከፍላጐት በላይ ነው፣ ከመውደድና ስራውን ለመጨረስ ካለ ፍላጐት በላይ ነው የተሰራው። አዎ ስራው የተሰራው ጥልቅ በሆነ ስሜት ውስጥ ነው። በዛ ስሜት ውስጥ ልዩ የሆኑ ነገሮች ይገኛሉ። በጥልቅ ስሜት ውስጥ ከፍተኛ ፍቅር አለ፣ ችሎታን የማዳበር ከፍተኛ ፍላጐት አለ፣ በዚህ ስሜት ውስጥ የምንፈልገውን የስራ ውጤት አሁን ካላገኘን ተስፋ መቁረጥ የሚባል ነገር ቦታ አያገኝም፣ እዚህ ስሜት ውስጥ ከውስጥ የሚገፋ ትልቅ ኃይል አለ። እናም ስራውን ለማሻሻል ያለመታከት አሁንም አሁንም ይሞክራል፣ ይሰራል። በዚህ ስሜት ውስጥ የሚሰራ ማንኛውም ስራ ደከመኝን፣ በቃኝን፣ አልችልምን፣ አይሆንምን፣ የመሳሰሉትን አያውቅም። የሚያውቀው ዛሬም መስራትን፣ አሁንም መስራትን ነው። በጥልቅ ስሜት ውስጥ ስራውን የሚያከናውን ሰው ምንም እንኳን ከማንም በላይ እየደከመ ቢሆንም፣ ከማንም በላይ እየጣረ ቢሆንም፣ ዛሬ ነገ ሳይል ሁሌ እየሰራ ቢሆንም፣ ሙሉ ሁለንተናውን ለዛ ስራ ቢሰጥም ይሄን ሰው አስተውሎ ላየ ግን በጣም ብዙ ቢሰራም ድካም ግን አይታይበትም። ቢታይበትም በውስጡ ባለው ፍቅር ተሸንፎ ወድቋል።

## አደጋ አይደለም

ይህን ጥልቅ ፍቅር ማንኛውም ዓይነት ስራ ውስጥ ልናገኘው እንችላለን። ሁሉም ስራ ላይ ግን አንድ ሰው ከፍተኛ የሆነ ጥልቅ ስሜት ሊኖረው አይችልም። በየደረጃው ስሜቶቹ ሊለያዩ ይችላሉ። ከፍተኛ ስሜት የሚወደውን ሰራ ያገኘ ሰው፣ ያ ሰው ብቻ ሳይሆን ስራውም የታደለ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በሌሎች ሁኔታዎች ውስጥ የማያገኛቸውን ዕድሎች ስራውን እያገኘ ነውና። በከፍተኛ ስሜት ውስጥ ሆኖ የተሰሩ ማንኛውም ስራዎች እስኪ እናስታውስ። የስዕል ፈጠራዎች፣ የሙዚቃ ስራዎች፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ የምርምር ስራዎች፣ ወዘተ። በጥልቅ ስሜት ውስጥ ሆኖ የተሰራ ማንኛውም ስራ፣ የስራው ውጤት

በድንገት የተገኘ አይደለም፡፡ ታስቦበት፣ ታቅዶበት እና ተሰርቶበት የተገኘ ነው እንጂ፡፡ ጥልቅ ስሜት የዛን ስራ ምርጥ የሆነን ውጤት ይወልዳል፡፡

## ስራውም ቢጠየቅ ያም ሰው ቢጠየቅ ...

የሚወደውን ስራ፣ የሚፈልገውን ስራ እና በትልቅ ስሜት ውስጥ ሆኖ ያን ስራ የሚሰራ ሰውን እና ያንን ስራ እንዴት እንደዚህ ሊሆን ቻለ? ብለን ብንጠይቃቸው መልሳቸው አንድ አይነት እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡ በምርጥ ሁኔታ እየሰራ ያለውን ስራ እና ሰሪውን ከሩቅ ሆኖ ለሚመለከት እንግዳ ነገር ሊሆንበት ይችላል፡፡ ከየት የመጣ ፍቅር ነው ይሄ ሁሉ ለስራ? ከየት የተገኘ ነው ይሄ ሁሉ ችሎታ? ከየት የተገኙ ናቸው እነዚህ ነገሮች? እነዚህን ጥያቄዎች በጥልቅ ስሜት ውስጥ ሆኖ የሚሰራውን ስራ የሚሰራ ሰው ሲሰማ ለእሱም እንግዳ ነው የሚሆንበት፡፡ ምክንያቱም ውስጡ ላለበት ሰው ጥያቄዎቹ ምን ማለታችሁ ነው ያሰኛል፡፡ ያ ሰው የሚያውቀው ገና የሚሰጠው ብዙ ፍቅር እንዳለ ነው፣ ገና የሚሰራው ብዙ ስራ እንዳለ ነው፣ ገና የሚያሻሽለው ብዙ ነገር እንዳለ ነው፣ ወዘተ፡፡ ስለዚህ ስራውም ቢጠየቅ የሚወደኝና የሚፈልገኝ ሰው ስላገኘኝ ነው ይላል፣ ስራውም ቢጠየቅ የምወደውና የምፈልገው ስለሆነ ነው ይላል፡፡

## ሁሉም ነገር ላይ...

ይህን ጥልቅ ስሜት ከስራችንም ውጪ ሌሎች ነገሮቻችንም ላይ ቢኖር ሁሉም ቢሆን የማይጠበቅ ውጤት ነው የሚኖረው፡፡ መልካም በሆነ ጠንካራ ስሜት ውስጥ ሆነን የምናከናውነው ማንኛውም ነገር ውጤቱ ራሳችን ከምንጠብቀው በላይ ነው፡፡ በጥልቅ ስሜት የተገነባ ትዳር በፍቅር የተንበሸበሸ ነው፣ በጠንካራ ስሜት ውስጥ ሆኖ የተገነባ እና የሚገነባ ጓደኝነት ለሁሉም ነው፣ በከፍተኛ ስሜት የተጠና ጥናት ውጤቱ ያማረ ነው፣ በከፍተኛ ስሜት ውስጥ ሆነን የምንጫወተው ማንኛውም ጨዋታ የማሸነፍ ዕድላችን ዝም ብለን ከምንጫወተው ይልቅ ሁሉም ቢሆን የላቀ ነው፡፡ የመሳሰሉት፡፡ ሁሉም ነገሮች ላይ ጥልቅ የሆነ ከውስጥ የመነጨ ስሜት ሲኖር ከእኛም አልፎ ተርፎ ለሌሎች የሚደርስ፣ ለዘመናት የሚሻገር እና ሁሉም ሲታወስ የሚደነቅ እና የሚመሰገን ስራ ይሰራል፡፡